# ምዕራፍ 11

## ሕይወት በሽበት፤

### ጡረታ መውጣት

በUBS (የመጽሐፍ ቅዱስ ማህበሮች) አንድ ሰው ቢያንስ 25 ዓመት ቢያገለግልና ዕድሜው 60 አመት ሲሆነው ጡረታ ሊወጣ ይችላል። በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ለሰባት አመትና ናይሮቢ ላይ ለአስራ ዘጠኝ ዓመት ያገለገልኩት ሲቆጠር ሃያ ስድስት ዓመት ይሞላል:: ግንቦት 22/1985 እድሜዬ ስልሳ ስለሚሞላ በዚያን ቀን ጡረታ እንድወጣ እንዲፈቀድልኝ መጋቢት 1982 ለተደረገው አፍሬክ አመለከትሁ። አንዴ ለምን ገና አቅም አለህ፤ ጡረታ መውጣት አይገባህም ያሉም አባላት ነበሩ። በመጨረሻ ግን ለብዙ አመታት በዚህ በከፍተኛ ደረጃ በማገልገሌና ጡረታ መውጣት መብቴ በመሆኑ ጥያቄዬን ተቀብለው እኔን የሚተካ እንፈልግ አሉ።

ቀደም ብዬ (65 ዓመት ሳይሆነኝ) ጡረታ እንድጠይቅ የገፋፉኝ ሁለት ምክንያቶች ናቸው:: አንዱ በእዚህ በከፍተኛ ደረጃ ለ17 አመት በማገልገሌ ሳልቀደም ልቅደም የሚል ሃሳብ ነው። የኔ አቻ የሆነው የአሜሪካው ዋና ጸሃፊ ባልጠብቀነው ምክንያት ጡረታ እንዲወጣ ተጠይቆ ነበር:: ይህ ሁኔታ በእኔም ሊደርስ ይችላል የሚል ስጋት ነበረኝ።

ሌላው ምክንያቴ ሁለት ማህበራት ነበሩ:: የናጀሪያና የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበሮች። ናይጀሪያ ከማንነታቸው የተነሳ ሲሆን የኢትዮጵያ ችግር ግን አወቅሁሽ ናቅሁሽ ነበር። እኔ ለአፍሪቃ ሃላፊ በነበርኩበት ዘመን ለናይጀሪያ አራት ዋና ጸሃፊዎች አሹሜአለሁ። የሚያስገርመው የመጨረሻው ጸሃፊ እኔን የተካው ሆነ።





አቶ ኃይሉ ወደ ናይሮቢ ከመጣ በኋላ ከኢትዮጵያ ጋር ያለኝ አታካራ ብዙ ነበር:: ዋናው ግጭቱ መተዳደሪያ ደንቡን መለወጣቸው ነበር። የቀድሞው መተዳደሪያ ደንብ ስለ ቦርድ አባላት የሚደነግገው፣ "ጠቅላላ የቦርድ አባላት ብዛት 24 ይሆናል፤ እነርሱም ከልዩ ልዩ ቤተክርስቲያን የተውጣጡ ይሆናሉ፤ በቦርድ ላይ ከአንድ ቤተ ክርስቲያን ከ 30% በላይ መሆን አይገባቸውም" ይላል። ይህን ለውጠው "የቦርድ አባላት አንድ ሶስተኛ ከኦርቶዶክስ፣ አንድ ሶስተኛ ከፕሮቴስታንት፣ አንድ ሶስተኛ ከካቶሊክ" መሆን አለበት በሚል ለወጡት። ይህን ለመለከት ያለንን ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ በመላክ "እንዲህ ልታደርጉ አይገባም" አልኳቸው።

አንደኛ የቦርድ አባላትን ስብጥር ብዛት የሚወስነው የአባላት ብዛት ነው፤ (በዚያን ጊዜ አብዛኛዎቹ የማህበሩ አባላት ከወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያን፣ ጥቂት ከኦርቶዶክስ በጣም ጥቂት ከካቶሊክ ነበሩ):: ሁለተኛ የኢትዮጵያ ህዝብ አብዛኞቹ ኦርቶዶክስ ቢሆንም ካቶሊኮች ግማሽ ሚሊዩን ይደርሳሉ፣ በዚያን ጊዜ መካነ የሱስ አንድ ሚሊዮን ተኩል፣ ቃለ ሕይወት አንድ ሚሊዮን ተኩል ሲሆኑ ሌሎች ፕሮቴስታንት ሲጨመሩ ከካቶሊክ ይበልጣሉ:: ሶስተኛ ማህበሩን በመደገፍም አንፃር ቢሆን ከወንጌላውያን ቤተክርስቲያን ብዙ ድጋፍ አለ:: ከካቶሊክ ትንሽ የሚገኝ ሲሆን ከኦርቶዶክስ ምእመናን ትንሽ ቢገኝም ከኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ምንም አይገኝም አልኩ። በዛ አመት ከየቤተክርስቲያኑ የተገኘውን ጠቅስሁ። ይህ ኦርቶዶክሳውያንን በጣም ሳያናድድ አልቀረም።

ለUBS ዋና ጸሃፊ (General Secretary) አዲስ ሰው ተሹሞ ነበር:: ይህ አዲሱ ዋና ጸሃፊ ለAFREC ስብሰባ ወደ ናይሮቢ ሲመጣ "ወዳንተ ልመጣ ስለሆነ የማን አገር መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ልጎብኝ?" አለኝ:: እኔም ከሚጎበኛቸው አንዷ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ልትሆን ይገባል ብዬ ሊጎበኝ ወደ ኢትዮጵያ መጣ:: በዚያን ጊዜ የማህበሩ ሊቀመንበርና ተጠባባቂ ዋና ጸሃፊው ኦርቶዶክሳውያን ነበሩ:: አዲሱ የUBS ዋና ጸሃፊ እንዲጎበኝ ከተደረገው አንዱ ተቋም ቤተ ክህነት ነበር። እዚያ የሄደው ፓትርያርኩን ሊጎበኝ ስለሆነ

ቁጸ.እነታቸው ጋር ሲሜወት "ቅሬታ አለን ብለው ቅሬታቸውን ገለጹ"። ቅሬታቸውም "ናይሮቢ ያለው ሰውዬአችሁ ቤተክርስቲያናችንን አይወድም፤ የምታስተምረውንም ይቃወማል። በማህበራችን ሥራ ጣልቃ ይገባል። ልጃችን እንዲሾም አይፈልግም"። የምንፈልገው አይነት መጽሐፍ ቅዱስ አይታተምልንም" አሉት።

አንድ የUBS ከፍተኛ ባለስልጣን እንደዚህ ያለ ክስ በእኔ ላይ ከአንድ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን የበላይ ሲሰነዘር ምን ሊሰማው እንደሚችል መገመት አያዳግትም። ናይሮቢ እንደደረሰ ለእኔና ለእንግሊዛዊው የበላይ የUBS አለቃዬ ነገረን። በነገሩ በጣም አዘንሁ።

ምን እናድርግም ዘንድ መመካከር ጀመርን። ሰማንያ አሃዱ የሚባለውን በደንባችን መሠረት ተጨማሪዎቹን መጻህፍት በሁለቱ አዲስ ኪዳኖች መሃል አድርገን በቤተክርስቲያናቸው አትሮኖስ ላይ አድረገው የሚያነቡት 2000 እሳትምን በስጦታ እንድናበረክት ተስማማን። በደንባችን መሠረት አንድ ቤተክርስቲያን (በተለይ በአውሮፓ ያሉ እርቶዶክሶች) የሚፈልጉት መጽሐፍ ቅዱስ ካለ በሕትመት ወጪው ተሳትፈውበት ለእነርሱ ብቻ እናሳትማለን የሚል ነው። የእኛዎቹ ለማሳተሚያ (እርዳታም ስለጠየቁ) ሳንድ ጊዜ ብቻ እናሳትምላቸው ተባባልን:: ይህንኑ ነገርኳቸው። በአዲስ ኪዳን ዉስጥ አንዳንድ ለውጥ አድርገው ከእነ ተጨማሪዎቹ ጋር ሰጡኝ። ተጨማሪዎቹ የታወቁና ከአሁን ቀደም የታተሙ ነበሩ።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከግዕዙ ጋር ለማስማማት ያደረጉትን ለውጥ እኔና በቢሮዬ የነበረ ካሳሁን ደጉ የሚባል ኢትዮጵያዊ ጋር አየን፤ ተነጋገርንበት። አዳዲስ መጻህፍትን ለህትመት የሚያዘጋጅ ስለሆነ ምን እናድርግ ተባባልን:: የለወጡትን በግርጌው 'ግሪኩ እንዲህ ይላል' በማለት ስናልፈው፣ ልናልፈው ያልቻልነው ማቴ 5፥6 የለወጡት ነበር። 'ጽድቅን የሚራቡ' የሚለውን 'ስለ ጽድቅ የሚራቡ' ብለው ነበር ያመጡት።





በተለይ ስለዚህ ጥቅስ ከዶክተር ምክረ ጋርም ተነጋገርሁ፤ በግርጌው ግሪኩ የሚለው እንዲህ ነው የሚል ቢያስቀጡም ትክክለኛውን አስቀምጠን በግርጌ ግእዙ የሚለው እንዲህ ነው ብለን አስቀምጠን እንዲታተም አደረግን። በዘህ ውሳኔዬ ካሳሁን አልተስማማም ነበር። እኔ የፈቀድኩት በትልቁ መጠን በስጦታ የምንሰጣቸውን 2000 እትም ብቻ ነበር:: ለወደፊቱ ሲታተም እነርሱም በወጪው እንዲሳተፉ በማድረግ እንደሚታተምላቸው በማሰብ ነበር:: ከዛ በኋላ ግን እኔ ከቦታው ስነሳ ይህ ሰማንያ አሃዱ መጽሃፍ ቅዱስ በብዛት እየታተመ በመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር የሚገኝ ሆነ:: ካሳሁን የፈራው ነገር ደረሰ፤ እየተፈጸምም ነው። ስለቀሩት የክስ ዝርዝሮች የተወሰደውን እርምጃ መዘርዘር ይህቺን ታሪኬን ስለማይጠቅም ትቼዋለሁ።

እኔም በራሴው ጠያቂነት ጡረታ መውጣቴ አይቀሬ መሆኑን ስገነዘብ የጡረታ ዘመኔን እንዴትና የት እንደማሳልፍ ማሰብ ጀመርሁ:: የት የሚለውን ለመመለስ ጊዜ አልፈጀብኝም:: ግደይ እዚያው ኬንያ መኖር ብንቀጥልስ ብላ ነበር፤ አሜሪካ ለመኖር ፈቃድ ማግኘት ከባድ ቢሆንም ልጆቻችን ወደ እነርሱ ብንሄድ እንደሚፈልጉ እናውቃለን:: ትልቁ ጥያቄ በቀረው ህይወቴ ምን ላድርግ? በቤተ ክርስቲያንስ በምን አገልግሎት ልሰማራ የሚለውን መመለስ ነበር:: ምላሹ ወሳኝ ነበር።

አንዱ ያሰላሰልኩት ነገር ወደ አገር ቤት ተመልሼ በአንድ ለቤተክርስቲያን ድጋፍ ሰጪ ሥራ ላይ በመሰማራቱ ላይ ነበር:: የምሰራው ስራ ለጌታ ሥራ ጊዜ የሚሰጠኝ መሆን አለበት ብዬም አሰብኩ።

***

## ሽግግር

ጡረታ መውጣት እንደምችል ከተረጋገጠ በኋላ እኔን የሚተካ ሰው መፈለግ ተጀመረ።የሚተካኝም ተመረጠ:: በእኔ ምትክ የተመረጠው ሰው ሥራ የጀመረው ከ እ.ኤ.እ ከሐምሌ 1 ቀን 1993 ጀምሮ ሲሆን የቅብብሎሽ ጊዜ እንዲኖር የእኔ

ጡረታ ቀን የሚጀምረው እ.ኤ.እ መስከረም 1 ቀን 1993 ነበር፡፡

እንደመጣ ቢሮዬንና ወንበሬን ሰቅቄስት በአጠገቡ አንዲት ቢሮ ዉስጥ ገባሁና በል ጀምር አልኩት፡፡ የተካኝ የናይጀሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ዋና ጸሃፊ የነበረው ከመሆኑም በላይ በዚያን ወቅት የአፍሬከም አባል ስለነበር ሥራው ምን እንደሆነ ያውቃል፡፡ የሚቀረው ያንን በተግባር ማዋል ነው፡፡ የቢሮ አሠራራችንን እያጠና ከውጭ ለሚመጡ ደብዳቤዎች መልስ መስጠት ጀመረ። ያሳንዳች ቅሬታ በፈለገው ጊዜ ወደ እኔ እየመጣ እንዲጠይቀኝ ተስማማን፡፡ እኔም እዚያቺው ቢሮ ሆኜ ስለእያንዳንዱ አገር የመጽሐፍ ቅዱስ ሥራ ሊከታተል የሚገባውን በጽሁፍ አዘጋጅቼ ሰጠሁት።

የእኔን ጡረታ መውጣት ለማክበር ልዩ ልዩ ግብዣዎች ተደርገውልኛል፡፡ በሰኔ ወር ዉስጥ ከሁሉም የአፍሪቃ ማህበሮች የመጡ ዋና ጸሃፊዎችና በናይሮቢ ግንኙነት ካለን የክርስቲያን ድርጅቶች ባሉበት ታላቅ መሸኛ ተደርጎልኝ ነበር። በዚያን ሰት ከተበረከቱልኝ ስጦታዎች አንዱ ከልዩ ልዩ ማህበሮችና የUBS ባለስልጣናት፣ ቀጥታ ግንኙነት ካለኝ ከአፍሪቃ ዉጭ ካሉ የመጽሀፍ ቅዱስ ማህበሮች እንዲሁም የሥራ ባልደረቦቼ የተጻፉልኝ የመሰናበቻ ደብዳቤዎች "የሚሊዮን በሰጠ መታወሻ TRIBUTE TO MILLION BELETE" በሚል በቆዳ ሽፋን ጠርዘው ሰጡኝ፡፡ ከየአገሩ ከመጡልኝ ስጦታዎች ይህ ትልቁ ስጦታዬ ነበር።

ሌላው ልጠቅሰው የምፈልገው ስንብት በመስሪያ ቤታችን ትንሽ ሁለገብ አዳራሽ የተደረገልኝን ነው፡፡ በመስሪያ ቤቴ አንድ ጥሩ ባህል ነበረን፡፡ ሰምሳ በተመደበልን 45 ደቂቃ ጊዜ ሁሉም ወደ ዉጭ እየሄደ ምሳውን ይበላ ነበር፡፡ ጊዜው አጭር ስነለበር ሁሉም ሰው ይጥሰዋል፡፡ ባንድ ወቅት አንዲት አሜሪካዊት ጠቃሚ ሃሳብ አቀረበች፡፡ "ምሳ ስመፈለግ ወደ ዉጭ ከምንወጣ ገንዘብ እናዋጣ መስሪያ ቤቱም ይጨምርበትና የሳንድዊች ምግቦች ተገዝተው ይቅረቡ፡፡ የ15 ደቂቃ ጊዜ ይሰጠንና ሁሉ ከየቢሮው ወጥቶ ወደ ሁለገብ አዳራሿ በመምጣት ሰራሱ ሳንድዊች አዘጋጅቶ ይብላ፡፡ ማታ የምንለቀቅበት ሰዓት በ30 ደቂቃ ይቅደምልን።





በዚያን ሰአት የፈለገ ይውጣ ወይም መሥራቱን ይቀጥል፡፡ ይህን ብናደርግ መስሪያ ቤቱ ሰምሳ ሠራተኞች የሚያጠፉትን የጊዜ ብክነት ያድናል" አለች፡፡ በነገሩ ተስማማንና ጀመርነው፡፡ ወደ ኋላ ምግብ እየተሠራ እንዲቀርብልንም አደረግን፡፡ ከጊዜ በኋላ ምግብ የማቅረቡን ሥራ የኔነሽ የምትባል ኢትዮጵያዊት ትሰራልን ነበር። ያ የምሳ ጊዜ ለመስሪያ ቤቱ ከመጥቀሙም በላይ ለእኛ ለሰራተኞች አብረን ህብረት የምናደርግበት ጊዜ ሆኖልን ስለነበር እንወደው ነበር። የቅርብ የሥራ ጓደኞቼ ለእኔ መሰናበቻ የዘጋጁት በዚህ ጊዜ ነበር።

የኔነሽ ለየት ያለ ምግብ እንድታዘጋጅ ተጠየቀች፡፡ ከተመገብን በኋላ ሶስት ሰዎች ጠቅላላውን ሰራተኛ ወክለው እንዲናገሩ ተደረገ፡፡ ሶሥቱም ምን አይነት መሪ እንደነበርኩ ልቤን የሚነካ ዲስኩር አደረጉ፡፡ በመጨረሻ አዲሱ አለቃም "እኔም እንድናገር ሊፈቀድልኝ ይችላል?" ብሎ ጠየቀ። "እዎ እዎ" ብለው ፈቀዱለት፤ ብድግ አለና "የሚሊዮንን ጫማ እንዳደርግ ተጠርቼአለሁ፤ ጫማው ተሰቀብኝ። ሚሊዮንን በመጠኑ አውቀዋለሁ፤ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ዓለም ያስገበኝ እርሱ ነው፡፡ መጥቼ እዚያች ቢሮ ከተቀመጥሁ ቀናት እየተቆጥሩ ነው፤ ሚሊዮን ሥራውን በደንብ ከማቀናበሩ የተነሳ ሥራው በደንብ እየሄደ ነው፤ እናተም ወደ እኔ አትመጡም፤ የምሰራው ሥራ ያለ አይመስልም፤ የኔ ድርሻ ምንድነው እያልኩ ነው?" ብሎ እሞግሶ ተቀመጠ። አባባሉ እኔኑ አስገረመኝ፤ ሥራቸውን እንዲሠሩ የእኔ ፊርማ የሚያስፈልገው በጣም ውስን ለሆኑ ጉዳዮች ነበር፡፡ ሁሉም ሃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ እኔ ብቻዬን ሳልሆን ከሥራ ጓደኞቼ ጋር ሆነን የአንዱ ሥራ የሌላውን እንዲቆጣጠር፣ ያንዱ ሥራ በሌላው ላይ የሚደገፍ እንዲሆን አድርጌ በማቀናበሬ እውነትም ያለ እኔ ሥራዎቹ ይሄዱ ነበር፡፡ ለሶስት ወር ትምህርት ወደ አሜሪካ በሄድኩበት ወቅት 'የዓለቃ ያለህ!' አልተባለም ነበር፡፡ ሥራዎች በሚገባ እየተሠሩ ጠበቁኝ። 'ሰካ ኅበዝ አቀናባሪ መሪ' ነበርሁ አልኩኝ። እግዚአብሔርን ለሰጠኝ ጥበብ አመሰገንሁት፤ አሁንም አመሰግነዋለሁ።

ተተኪዬን በማለማመድ ላይ እያለሁ ወደ አገሬ እንዴት እንደምመለስ ማሰቤንም ቀጠልኩ፡፡ ወደ አገሬ ስመለስ ምን አደርጋለሁ? በአየር ወይስ በየብስ? እቃችንን

በሚገባ ጠፍረን ኬንያ ባለው ወዳጃችን አቶ መስፍን ኤልያስ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ባለስልጣን ባገኘነው ልዩ ቅናሽ አማካኝነት በአየር ልከናል፡፡ የቀረነው እኛ ነበርን፡፡ በዚያን ሰሞን ኔልሰን ማንዴላ ከ27 አመት እስር የተለቀቀበት ጊዜ ነበር፡፡ "ከእስር ቤት የምወጣው በእግሬ እየተራምድሁ ነው" ብሎ ነበር። (Walk out of prison) እኔም ወደ አገሬ የምገባው በአየር ሳይሆን በሞያሌ በኩል በመንገድ መሆን አለበት ብዬ ነበር፡፡ የገዛኋት ኢይሱዙ የመስክ መኪና ለዚህ ስለምትመች አብሮኝ የሚጓዝም ሰው አዘጋጀሁ፡፡ ይህን ዉሳኔዬን የሚቃወም በዛ፡፡ በዚያን ጊዜ በመንገድ ላይ ሽፍቶች አሉ እየተባለ ይወራ ነበር፡፡ ስለሚፈሩ አልፎ አልፎ የግል መኪናዎች በአጀባ ይሄዳሉ ይባላል። ጳውሎስ ጉልላት "ምንም ላይደርስብህ ይችላል፤ ቢሆንም በሰዎች አፍ ስለገባህ በአየር ብትሄድ ይሻላል" አለ፡፡ ከተቃዋሚዎች አንዱ ናታንም ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ እዚያው UNEP የሚባል መስሪያ ቤት ዉስጥ ጊዜያዊ ሥራ አግኝቶ ይሠራ ነበር፡፡ አንድ ቀን ከቢሮው ደውሎ "ከካይሮ እስከ ኬፕታውን መኪና በመንዳት የተጓዙ ሰዎች አገኘሁ፡፡ እነኚህ ሰዎች በጉዞአቸው ወቅት አደገኛው ቦታ የትኛው እንደሆነ ነገሩኝ፡፡ እርሱም በሞያሌና በማርሳቤት መሃከል ያለው ቦታ አደገኛ ነበር አሉኝ" አለ፡፡ በየብስ መንገድ አትሂድ ለማለት ያሰው ነበር፡፡ ላልሄድ ቀረሁ። በተመደው መንገድ በአየር አገሬ ገባሁ።

## ለኢትዮጵያ ምን ልናደርግ እንችላለን?

ናይሮቢ የምንኖር ወንድሞች በተገናኘን ቁጥር የምናወራው ስለ አገራችን ነበር። አንድ ቀን ዶክተር አለሙ ማሞ አስቲ በሃገራችን አንድ ነገር ስለማድረግ እንወያይ፣ ራእይም ይኑረን፤ አቁበም ባንለው ትንሽ ገንዘብ ማዋጣትም እንጀምር አሰን። ተስማማን። በውይይታችን የምንሰራው ስራ ቤተ ክርስቲያንን የሚጠቅም መሆን አለበት ተባባልን፡፡ የሚመሠረተው ድርጅት እራሱን የሚችል መሆን ስላለበት የንግድ መልክ ያለው ሊሆን ይገባል አልን፡፡ በየወሩ ትንሽ ገንዘብ እናዋጣም ተባባልንና አቶ ኃይሉን ገንዘብ ያዥ አደረግነው።





ይህን እያደረግን እያለ እኔ ጡረታ ወጥቼ ወደ ኢትዮጵያ የመመለሴ ነገር መልከ እየያዘ መጣ፡፡ የቀድሞው የሚኖ መጻህፍት ቤት አገልግሎት ትዝ አለኝ፡፡ ይህ መጻህፍት መደብር ብቸኛው የክርስቲያን መጻህፍት ከውጭ አስመጪ ነበር፡፡ ልዩ ልዩ ትናንሽ ጽሁፎች በጅምላ ይሸጥ ነበር፡፡ ይህ በቀጥታ ቤተ ክርስቲያንን የሚያግዝ ሥራ ነው፡፡ የመካነየሱስ ማጻህፍት መደብር መኖሩን ተረዳሁ፡፡ ይህ መደብር የሚያስራጨው ውሱን (Dinominational) መጽሃፍ እንደነበርም አስተዋልሁ፡፡ በመሆኑም ሁሉንም አብያተ ክርስቲያናት የሚያገለግል ሆኖ አላገኘሁትም። በተጨማሪ አገልጋዮች የሚሰብኩትን ለማሳተም ቢፈልጉ የገንዘብ አቅም እንደሌላቸው ስገምት የአሳታሚነት ሥራ ብልጭ አለቺብኝ፡፡ ይህንኑ ለወንድሞቼ አካፈልኳቸው። ግፋበት አሉኝ።

## የራዕይ መጻሕፍት መደብር እና አሳታሚ መከፈት

አዲስ አበባ መኖር እንደጀመርኹ የክርስቲያን መጻህፍት መደብር የመከፈቱን ሥራ ጀመርኹ። ራእይን ለመከፈት ያሳለፍኩት ዉጣ ውረድ አስቸጋሪ ነበር። አልተርከውም፡፡ ባለሥልጣናት የኔ ብጤው ወደ ቢሮአቸው ሲሄድ በመርዳት ፋንታ "አይቻልም" ለማለት ወንበራቸው ላይ የተቀመጡ ይመስላል። ራእይን በመጀመር ትልቅ የምክር አገልግሎት በመስጠትና የመጀመሪያው ቦርድ ሊቀ መንበር በመሆን ያገለግለው አቶ ሽፈራው ወልደሚካኤል ነው። የህግ አማካሪ ድርጅት ስለነበረው የራዕይን መመስረቻ ጽሁፍና መታዳደሪያ ደንብ አሰረቅቆ በኩባንያ መልከ ሥራችንን እንድንጀምር አደረገን፡፡ ራዕይ ባለብዙ ዘርፍ ኩባንያ ሆኖ ተቀርጸ፡፡ መጽሐፍ፣ ጋዜጣ ከውጭ ለማስመጣት የሚችል፣ በአገር ቤትም ማሳተምና ማተሚያ ቤትም ለማቋቋም እንደሚችል ተደርጎ መተዳደሪያና መመስረቻ ጽሁፉ ተዘጋጀ።

የመጀመሪያው ዳገት ሱቅ ማግኘት ነበር። መንገድ ዳር ሱቅ እንደማላገኝ አወቅሁ። ስለዚህ ከዋናው መንገድ ገባ ብዬ ቤት ፈለግሁ፡፡ አራት ኪሎ

የቀድሞ ሁለተኛ ፖሊስ ጥቢያ ጎን አንድ መጠገን የሚያስፈልገው በግቢዉ ዉስጥ ክፍሎች ለማሰራት የተጀመረ ቤት አገኘሁ። አንዲያከራዩኝ ስጠይቅ ዋጋውን ነግረውኝ ያሙት ኪራዩን በቅድሚያ አድክፍል ጠየቁኝ። ስለከፍያውና አከፋፈሉ ተስማማን። ቤቱም እንዲታደስ፣ የተጀመሩትም ክፍሎች ለቢሮና ለግምጃ ቤት ስለሚያስፈልጉ ቶሎ እንዲሠሩ የመጀመሪያ ቀብድ ሰጠሁና ሥራው ተጀመረ።

ገና ሱቅ መፈለግ ስጀምር አቶ መኩሪያ በአስቴዲዩም አካባቢ ለባለቤታቸው ተከራይተው የነበረውን የሻይና ቡና መሸጫ ሊያከራዩኝ ተጠቁሜ ጠየኳቸው። እርሳቸውም ቀድሞ የተከራየው ሰው ያስበው ነገር አለው፤ እርሱን ላጣራ እና ላንተ አከራይሃለሁ አሉኝ። ሰውየው ሲጠየቅ እንኳን ሊወጣ ቤቱ ለእኔ ይገባል አልወጣም ብሎአቸው ክርክር ዉስጥ ገቡ። ጉዳዩም ወደ ፍርድ ቤት ሄደ። ስለዚህ ያን ቤት የማግኘቴ ተስፋ ስለመነመነ ተውኩት። የአራት ኪሎውን ሱቅ እንደተከራየሁ፥ አንድ ቀን አቶ መኩሪያ ጅማ ደወሉና ሰውዬው እንደማያዋጣው ለለተረዳ ቤቱን ሊያስረክበኝ ነው፤ ልትወስደው ትችላለህ አሉኝ። አንድ ሱቅ ከማካሄድ ሁለት ለምን አይሆንም ብዬ ይህንም ሁለተኛ ሱቅ ላደርገው ወሰንሁ።

ሁለቱም ለመጽሐፍ መሸጫ እንዲሆኑ መደርደሪያዎች ስለሚያስፈልጋቸው ለሁለቱም አዘጋጀሁ። መደብሮቹን ለመክፈት ፈቃድ ማውጣት ጀመርሁ፤ ቦታዎቹን አስመዘገብሁ፤ በተጨማሪ እየተዘዋወረች የምትሸጥም መኪና እንዲኖረኝ አደረግሁ። ሥራ ተጀመረ፤ መኪናዋም በየአጥቢያውና የኮንፍረንስ ቦታዎች እየሄደች መሸጥ ጀመረች፤ ራዕይንም በሄደችበት ቦታ ሁሉ አስተዋወቀች፤ አጥቢያዎች በየግቢአቸው መጽሐፍ መሸጫ ኪዮስክ አዲከፍቱ አደፋፈርን፤ የኋላ ኋላ ኪዮስክ የከፈቱት መኪናችን ግቢአቸው አዳትደርስ አገዱ። ይህንን በማድረግ አባሎቻቸውን መበደላቸውን አለመገንዘባቸው አሳዘነኝ። ወደ ኮንፈረንስ ቦታዎች ራቅ ብሎ መሄዱ ብዙ ወጪ ስለጠየቀን አልቀጠልንበትም።

ራዕይን ማስተዳደር አያስቸገረኝ ሄደ፤ ትልቁ ችግሬ የመንግሥት አሠራር ነበር። አንድ መሥሪያ ቤት ስሄድ እንዲህ አድርግ ወይም ያን አምጣ ይሉኛል።





ይህ ለምን ያስፈልጋል ብዬ ስጠይቅ መልሳቸው 'ደንቡ ስለሚል' ይሉኛል፤ የመሥሪያ ቤታቸው ደንብ መሆኑ ነው። በአንድ ወቅት ወደ አንድ መሥሪያ ቤት ሄጄ ጉዳዬን አቅርቤ ስጨርስ ለሰጡኝ ምላሽ ለምን? ብዬ ማብራሪያ ስጠይቅ የተለመደ መልሳቸው ትዝ አለኝና የሚናገሩትን ከመስማቴ በፊት 'ደንቡ ስለሚል እንዳትሉኝ' አልኳቸው። 'እርሶን የመሰለ ሰው እንዴት ከደንብ ዉጪ እንድንሠራ ይፈልጋል?' ብለው ማመልከቻዬን መለሱልኝ። እውነት ነበራቸው። ብዙ ነገር በአነርሱ በአስፈፃሚዎቹ አይፈታም፤ "መልካም ፈቃድዎ ይሁንና አለቃዎን ላናግር" አልኩኝና የአለቃቸውን ቢሮ አሳዩኝ። አለቃው ቢሮ ስገባ ናይሮቢ የነበረ የምንተዋወቅ ሰው ሆኖ አገኘሁት። ከእርሱ በፊት የነበረው አለቃ ያወጣው ደንብ መሆኑን ነግሮ ጉዳዬን ፈጽሞ ለቀቀኝ።

የእኔ በየቢሮው በመሄድ የምገጥመኝን እታካራ የተረዳችና የእኔ አካሄድ ለእኔ ልክ ቢመስልም እንደማያዋጣኝ በማሰብ ጉዳይ አስፈጻሚ እንድቀጥር እህት ብጹአን አማረ መከረቺኝ። ከምክር አልፋም ሰው ጠቆመቺኝ። በቅርብ ጊዜ ከሰባት አመት እስራት ተፈቶ የወጣውን ሻምበል ንጋቱ በጋለን ነበር የጠቆመችኝ። እርሱ በአጭር ጊዜ የራዕይን ዓላማ አውቆ ከብዙ ችግር ገላገለኝ። ሁለት ዓመት እንደሠራ ሌላ የተሻለ ደሞዝ የሚከፍለው ሥራ በማግኘቱ የፖሊስ ሻምበል የነበረውን አቶ ፊሊጶስ አቡላን ተክቶልኝ ወጣ። ንጋቱ ብዙም ሳይቆይ ዲቪ አግኝቶ ከቤተሰቡ ጋር ወደ አሜሪካ ነጎደ።

## የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት

ከናይሮቢ ከመጣሁ በኋላ በዙ ጊዜ ወጣት የመሠረተ ክርስቶስ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ወደ እኔ መጥተው "የአዲስ አበባ መሠረተ ክርስቶስ መቼ ተጀመረች"? ብለው ይጠይቁኛል። መሠረተ ክርስቶስ እራሷ መቼ ተጀመረች የሚለው አጠያያቂ ነው፤ መቼ ተደራጀች? ቢባል ቀላል ነው፤ ቤተ ክርስቲያን የአማኞች ስብስብ እንደመሆኗ፣ የመጀመሪያው አማኝ ማን ነው? ያ ሰው ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ የተቀበለው (ክርስቶስን መከተል የጀመረው)

መቼ ነው? ያቺ ቀን ቤተ ክርስቲያናችን የተጀመረችበት ቀን ነው ብንል ያዋጣል፤ ያን ቀን ማወቅ አስቸጋሪ ነው፤ መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የሜኖናይት ሚሲዮን አገለግሎት ውጤት ናት።

የመጀመሪያው አማኝ አቶ ባቲ አንሰርሙ የሚባሉ የኃ.ማ.ማ.መ.ሆስፒታል ዘበኛ መሆናቸውን ከዚህ በፊት ገልጫለሁ። እኚህ ሰው መቼ ጌታን ለመከተል ወሰኑ የሚለውን ማወቅ አልቻልንም፤ ቢሆንም በመሠረተ ክርስቶሰ ቤተ ክርስቲያን ደንብ መሰረት አንድ ሰው የቤተ ክርስቲያን አባል ሆነ የሚባለው ሲጠመቅ ነው። እኛ አናባፕቲስቶች ነን። መጽሐፍ ቅዱስ "ያመነ የተጠመቀ ይድናል" ስለሚል አንድ ሰው ከመጠመቁ በፊት ማምን አለበት፤ ስለዚህ የመጀመሪያውን ጥምቀት (በህፃንነታችን የተጠመቅነውን) አንቀበለውም። አቶ ባቲ መቼ እንዳመኑ ባናውቅም መቼ እንደተጠመቁ እናውቃለን፤ ያቺን ቀን የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ልደት ቀን ብለን ወስደናል፤ ያም ቀን ሰኔ 8 ቀን 1943 ዓ ም ነው።

ሜኖናይቶች በአዲስ አበባ አምልኮ ፕሮግራም የጀመሩበትን ቀን የአዲስ አበባ መሠረተ ክርስቶስ የተጀመረችበት ቀን እንደሆነ ብንቆጥር በአኔና በፀጋ ቅስቀሳ በመርሐ እውራን ት/ቤት አምልኮ የተጀመረበት ቀን ነው ልንል እንችላለን።

ቤተክርስቲያኗ በአዲስ አበባ ውስጥ እንድትጀመር እግዚአብሔር ምክንያት አድርጎ ተጠቅሞብኛል፡፡ በአጥቢያ ከመምራት አንስቶ እስከ አህጉርና አለም አቀፍ አመራሮች ላይ አገልግያለሁ፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥም ብዙ ተባርኬያለሁ፡፡

አሁን ጡረታ ወጥቼ ወደ አገሬ ከተመለስኩ በኋላ በተደጋጋሚ ይቀርብልኝ የነበረው ጥያቄ “እንግዲህ ምን ልታደርግ ነው?” የሚል ነበር፡፡ እኔም ስመልስ “ጋሼ የመባልን ክብር ልመገብ እንጂ ልቀጠር አልመጣሁም” እል ነበር፡፡ አንድ ቀን ሰሎሞን ከበደና በድሩ ሁሴን ይህንኑ ጥያቄ አቀረቡልኝ፡፡ የቤተክርስቲያን ሃላፊዎች መሆናቸውን በመገንዘብ፡ "እኔ ምንም አይነት ሃላፊነት ቦታ ውስጥ መግባት አልፈልግም፤ የቋሚ ኮሚቴ አባል ለመሆንም አልፈልግም፤ ሆኖም ጊዜያዊ ኮሚቴዎች (task force) ላይ ላገለግል ፈቃደኛ ነኝ አልኳቸው፡፡ ከዚህ ሌላ በቤተክርስቲያን ቋሚ ኮሚቴና የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ለመሆን





አልፈልግም ማለቴ ነበር፡፡ ጨምሬም "ሹመት እንገፍግፎኛል፤ ሹመት ማለት 'ሺ ሞት' ማለት መሆኑን በሚገባ ገብቶኛል አልኳቸው። የእነርሱ አላማ በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ (ሥ.አ.ኮ.) ላይ እንዳገለግል ነበር።

በመጀመሪያው አመት በሥ.አ.ኮ. ላይ እንደ ታዛቢ በመገኘት እንደ አማካሪ አገለግል ነበር፡፡ በድሩ ዋና ጸሃፊ ነው፡፡ ሰሎሞን ሰብሳቢ ነበር። በሥ.አ.ኮ. ላይ ብዙ ዘመን ስላገለገለ ማረፍ አለበት ብለው እኔ ለአንድ የአገልግሎት ዘመን እንዳገለግል አጥብቀው ጠየቁኝ፤ ወተወቱኝም፡፡ አቋሜን አስለቀቁኝና ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ላይ እንዳገልግል አደረጉ፡፡ ሥ.አ.ኮ. ላይ እንደገባሁ ሰብሳቢ ብለው ለአንድ አመት በሰብሳቢነት አገለገልሁ። በሚቀጥለው አመት ሰሎሞን እንደገና የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባል ሆኖ ሲመረጥ ወደ ሊቀመንበርነቱም ተመለሰ። በሥ.አ.ኮ. ላይ ሁለት አመት ካገለገልሁ በኋላ ደግሜ እንድመረጥ በማድረጋቸው የቤተ ክርስቲያኒቱ እቃቤ ነዋይ ሆንሁ፡፡ ትልቅ ትግል ነበር፤ ልዩ የአስተዳደር መመሪያ አውጥተን የመሠረተ ክርስቶስ ኮሌጅን ያቋቋምነው በዚህ ዘመን ነበር።

በቤተ ክርስቲያናችን ሁለት ወሳኝ ነን የሚሉ (እምባ ገነን) አካሎች አሉ። እነርሱም በዋናው ቤተ ክርስቲያን ሥ.አ.ኮ. ሲሆኑ፤ በአጥቢያ ደረጃ ደግሞ የአጥቢያ ሽማግሌ ጉባኤ ናቸው። ለስሙ ሁለቱም ተጠሪ የሚሆኑለት አካል አለ፡፡ ለሥ.አ.ኮ. ጠቅላላ መማከርት ጉባኤ (ጠመጉ) ሲሆን፤ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የመረጣቸው የአጥቢያ ምእመን ነው። እነኚህ ሁለት አካሎች የሚወስኑት ሳይፈተሽ (ከአለቆቻቸው ማንም ሳያየው) ውሳኔአቸው በሥራ ላይ ይውላል፡፡ እያንዳንዱ የሥ.አ.ኮ. ውሳኔ በጠ.መ.ጉ. መጽደቅ አለበት ባይባልም ውሳኔዎችን የሚያይ ቢያስፈልግ "ቆይ አስቲ" የሚል መኖር አለበት ባይ ነበርሁ።

የአጥቢያ ሽማግሌዎች ተጠሪነታቸው ለምእመኑ ነው ቢባልም ጊዜያዊም ሆነ ቋሚ ወስኔአቸው በአጥቢያው ምእመን የሚታይበት ምንም ዘዴ የለም። ተጠሪነታቸው የሚተገበርበት ዘዴ የለም፡፡ እነርሱ የወሰኑት ይሆናል። በሁለቱም አካሎች የማይታወጁ ውሳኔዎች አሉ፤ ለምሳሌ እንደ ደሞዝ ያሉት

ጉዳዮች፣ እንደነዚህ ያሉት በምስጢር ሊያዙ ይችላሉ ባይ ነኝ።

ይህን ለማሻሻል የሚያስችሉ ዘዴዎችን ጠቁሜ የሥ.እ.ኮ. አባልነቴን አጠናቀቅሁ። ይህ ባለመሆኑ በኮሌጁ የደረሰውን ትርምስ የሚያውቅ ያውቀዋል። በየአጥቢያዎችም እየተፈጸመ ነው። ለነኚህ መግለጫዎች ወይም ምሳሌ በመስጠት ታሪኬን አላስረዝምም።

ወደአገር ቤት ከተመለስሁ በኋላ የከበደኝና ያሳዘነኝም አሁንም እያሣሰዘነኝ ያለው የቤተክርስቲያን ፕሮግራም አካሄድ ነው፡፡ አላስፈላጊ ጩኸቶች፣ ልፍለፋዎች አሉ፡፡ እኔ በማንኛውም ጊዜ የምንናገረውን እስተውለን መናገር አለብን ባይ ነኝ። ለምሳሌ ሃሌ ሉያ ማለት እግዚአብሔር ይመስገን ማለት ነው፤ ይህ ቅዱስ ቃል ነው፤ ይህን ቃል በልዩ ልዩ የድምጽ ቃና፣ ቅላፄና መጠን በጩኸት ማለት ምን ማለት ነው? የምናስተውል ከሆነ "እግዚአብሔር ይመስገን" የሚለውን ቃል በጩኸት እንልም። ሃሌ ሉያን ግን እንለዋለን። ለጸሎት ተንበርከከን ደጋግሞ ደግሞ 'እንጸልይ .. እንጸልይ' ይባላል፡፡ እንደኔ እንደኔ ከመድረክ የሚነገረው ነገር ሁሉ ትርጉም ያለው መሆን አለበት ባይ ነኝ። ሌሎች ትርጉም የለሽ አባባሎችም አሉ።

ይህ ሁሉ ሊዋጥልኝ አልቻለም። አንድ ቀን የቀድሞ ወዳጄን በየነ ሙላቱን "የአምልኮ ስርዓቱን ቅጥ ማጣትና ስለ ጩኸቱ ምን ትላለህ? እንዴት ታየዋለህ?" አልኩት፡፡ "ለምደነዋል፤ የፈለጉትን ይበሉ እያልሁ አለሁ" አለኝ።

ከመድረክ ውሸት ሲነገር ያናድደኛል፡፡ በማንኛውም ጊዜ ዉሸት መናገር ተገቢ አይደለም፤ ኃጢአት ነው። ከአገልጋይ አፍ ሲወጣ ደግሞ ይበልጥ ያስፀይፋል። አንድ ጊዜ የአዲስ አበባ አጥቢያዎች ሁሉ ከንፍረንስ ላይ ተናጋሪ የሆነ አገልጋይ እንዲህ ሲል ሰማሁት፡-"እኔ ብዙ ጊዜ የማገለግለው ደቡብ ነው፤ እዛ 500,000፣ 400,000 ሰዎች በሚገኙበት ቦታ ነው የማገለግለው" አለ፡፡

የትኛው ከተማ ላይ ነው ይሄን ያህል ህዝቦች ለኮንፈረንስ የሚሰበሰቡት? አልሁ። እስኪ ሂሳቡ ይሰላ፤ ይህን ያህል ሰው የሚይዝስ ምን ዓይነት ቦታ አለ?





የአዲስ አበባ ስታዲዩም እንኳ መጫወቻውን ሜዳ ጨምሮ ከ200,000 ህዝብ በላይ አይሰበሰብም፡፡ አገልጋዩ ጨምሮም፡-"በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ወደ ጌታ ይመጣሉ፤ ከከፉ አጋንንት ይላቀቃሉ፤ ከህመም ይፈወሳሉ"አለ። አሁንም ያለው አልተዋጠልኝም፤ እንዲያውም አናደደኝ፤ ተነስቼ ወጣሁ፤ መኪናዬን አስነስቼ ከግቢ ወጣሁ፤ የት ነው የምሄደው? አልኩና፤ ተመልሼ ለኮንፍረንሱ መሪዎች "ምን አይነት ዉሸተኛ አገልጋይ ነው ያቆማችሁት?" ብዬ ከላይ ያነሳኋቸውን ነጥቦች ዘርዝሬ ቅሬታዬን አወረድኩባቸው።

አንዳንድ ለባኪዎች "ተፈውሳችኋል" የሚሉትን ማመን ያስቸግረኛል፡፡ በብዙ ምእመን ዉስጥ "ማህጸንሽን የሚያምሽ አንድ እህት አለሽ ተፈውሰሻል" ይላሉ። ሊሆን ይችላል፤ ብዙ ምእመን ዉስጥ የማህጸን ችግር ያለባቸው ሴቶች ብዙ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ዉስጥ የተፈወሰቺው 'እንዲት' የተባለቺው የቷ ትሆን? እላለሁ። ሌላው "ጌታ ተናገረኝ" ወይም "ይህ ይህ ይታየኛል" የሚሉት ናቸው፡፡ እንዲህ የሚሉትን በጽሞና እለማለሁ፤ ከቃሉ ጋር አነጻጽራለሁ፤ ነቢይ ነኝ ባይ ሁሉ ነቢይ እንዳልሆነ አውቃለሁ ቃሉ መርምሩ ይላል፡፡ ብዙ ጊዜ የሚሉትን የሚሉት "የመገለጥ ስጦታ አለው" እንዲባሉ ይመስለኛል። ብዙ ጊዜ እንዲህ የሚሉት ተጋብዘው የሚመጡት ናቸው። ይህንን ሂደት አሁንም እያለሁ።

ከናይሮቢ ስመጣ በየአጥቢያው ለስብከት እጋበዛለሁ የሚል ግምት ነበረኝ፡፡ እንደመጣሁ አልፎ አልፎ እድል ባገኝም በህይወቴ ያልሰበኩባቸው ጊዜያቶች ከናይሮቢ ከተመለስሁ በኋላ የኖርኩባቸው ናቸው፡፡ ለምን ይሆን ብዬ ስጠይቅ ሁለት መልስ አገኛለሁ፤ አንደኛው በቤተ ክርስቲያናቸው እንድሰብክ መንፈስ ስላላሳያቸው ነው፤ መንፈስ ጉድለቴን ስለሚያውቅ ይሆናል እላለሁ። ሁለተኛው እንደ እነርሱ በልሳን ስለማልናገርና በስብከቴም ደጋግሜ ሃሌ ሉያ ወይም እግዚአብሄር ይመስገን ስለማልል ይመስለኛል። አሁን አሁን እንደ ተመስከትኩት የማልጋበዘው እኔ ብቻ ሳልሆን አንደኔ ቀደም ብለው አገልጋዮች የነበሩም ናቸው፡፡ የእኛ አይነቶቹን የመጋበዝ ባህል ቀርትዋል።

አሜሪካ እየኖርሁ ስመለስ ብዙ ጊዜ የማመልከው ካራ መሠረተ ክርስቶስ

አጥቢያ ነው፡፡ ካራም እንዳገለግል አይጠይቁኝም፡፡ ወደ አሜሪካ ልመለስ ሰል አፍ አውጥቼ የማካፍለው አለኝ ብዬ ጊዜ ተሰጥቶኝ "ወጣቶች ስሙ" እያልሁ ወጣቶችን የሚመለከት መልእክት፣ "አዋቂዎች ስሙ" ባማለት በተለይ አዋቂዎችን የሚመለከት መልእክት አቀረብሁ፡፡ ጨርሼ እንደ ተቀመጥሁ አንድ ወጣት ጊዜ እንዲሰጠው ጠየቀ፤ ስለ ተሰማው መልእክት ግሩም ግጥም አሰማ፤ ተጨበጨበለት፡፡ አገልጋዩም ስላቀርብኩት ብዙ ምክር አዘል መልእክት አመሰገነና ብዙ ጊዜ እድል ባለመስጠቱ ቅሬታውን ገለጸ፡፡

ይህችን ክፍል ከመጻፌ ከሁለተ ቀን በፊት ከዚህ አገልጋይ ረጅም ደብዳቤ ደረሰኝ፡፡ በደብዳቤውም እንዲህ አለ፤ "ሊሄዱ አካባቢ ቃል እንዲያካፍሉን ጊዜ ሰጥተንዎት ነበር፤ በእጅጉ መባረኬን ስነግርዎት መቆጨቴንም ልገልጽልዎት እፈልጋለሁ፤ ምክንያቱም እስካሁን ከእርሶ ብዙ ልንማር ሲገባን ብዙ ጊዜዎችን ሳንጠቀም በማለፋችን ነው"።

## በምስራቅ አ.አ. መሠረተ ክርስቶስ አጥቢያ ሽምግልና

ከናይሮቢ እንደተመለስሁ የምኖረው ቦሌ አካባቢ በመሆኑ የምሥራቅ አ.አ. መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አባል ሆንሁ። የአጥቢያ ቤተክርስቲያንዋ አካሄድም የሚያሳስብኝ በመሆኑ ከውጭ ሆኜ ሂሰ ማቅረብ ሰላበዛሁ ሊሆንም ይችላል ሽማግሌ እንድሆን ተጠቁሜ በመመረጤ ከባድ ተግዳሮት ገጠመኝ፡፡ በሕይወቴ የማይግባባ ቡድን ያገጠመኝ ጊዜ ነበር፡፡ የምለውን በጥሞና የሚሰሙ የሚመስሉ ነበሩ፡፡ የሚሰጡ መልእክቶች በቃሉ ላይ የተመሠረቱ ከመሆን ይልቅ ከቅባት የፈለቁ እንዲሆኑ የሚፈልጉም ነበሩ፡፡ በአንድ ወቅት ባለፉት ሶስት ወራት መልእክት ያቀረቡት ስንት ከመሠረተ ክርስቶስ ስንት ከውጭ እንደሆኑና ከውጭ የተጋበዙት ከምን ከምን ቤተ ክርስቲያን እንደሆኑ የሚያሳይ አጭር ሰንጠረዥ አቀረብሁ፡፡ በመረጃው መሠረት ከቤተ ክርስቲያናችን የሰበኩት በጣም ጥቂት ነበሩ። ክርክር በመሃላችን ተነሳ፡፡ ክርክራችን አ. አ. መሰረተ ክርስቶስ ክልል የተሰማ ይመስለኛል። በዚህ ላይ ውሳኔ ሳንሰጥ የዋና ቤተ ክርስቲያናችን ጠ.መ.ጉ. ተደርጎ ነበር። ከምን ተነስተው እንደወሰኑ ባላውቅም የኛን አሠራር የሚመለከት ዉሳኔ ተወሰና፣ ዉሳኔው በመመሪያ መልክ ለአጥቢያችን መጣ፡፡

መመሪያው ለሁሉም የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አጥቢያዎች የሚከተሉት ነው። በዛ መመሪያ መሠረት በየቤተ ክርስቲያናችን አጥቢያዎች ከ25% በላይ ለውጭ እንዳይሰጥ የሚደነግግ ነበር፡፡ ያን መመሪያ እኔ እንደቀሰቀስሁ የወሰዱም ነበሩ። በመሃከላችን በተከሰተው አለመግባባት መሠረት ከልሉ በመሃከላችን ገቦቶ (ሊቀ መንበሩ ከእኔ ጋር ተማክሮ) ሁላችንም ከሽማግሌነት እንድንወርድ ተደረገ። የኔ በአጥቢያ ሽምግልና ማገልገል ጉዳይ በዚያ አበቃ።

## ካራ አጥቢያ ተሳትፎ

የአዲስ አበባ ቤታችን ሰፈር መኖሪያ ሰፈርነቱ እየቀነሰ እንደሚሄድ ስለገመትን ወጣ ያለ ቤት እንዲኖረን ተመኘን፡፡ እያት ለማስገንባት ወስነን ጀምረንም ነበር። ቦታም መረጥን፤ በትንሽ ነገር ባለመስማማታችን ከደቡብ አፍሪቃ መጡ ወደ ተባለው ሮፓክ ወደ ሚባለው አዲሱ የመኖሪያ ገንቢ ድርጅት ፊታችንን አዞርን፡፡ ከተማ ዉስጥ ወደአለው ቢሮ ሄደን መረጃ ካገኘን በኋላ ወደ ለገጣፎ ሄደን በ500 ካሬ ሜትር ላይ ለናሙና ያሰሩትን ቤት ተመለከትን፤ ያየናት ቤት ትንሽ ከመሆንዋም በላይ ኮሽ ሆና አገኘናት፡፡ ዋጋዋ በጣም ትንሽ በመሆኑ በዚህ ዋጋ ምን ይጠበቃል ብለን በ1000 ካሬ መሬት ላይ የሚሠራው ሰፋ ያለውን ቤት ዋጋ ጠየቅን ስለተስማማን አሠራሩም በጣም እንደሚሻል ተነግሮን መመዝገቢያ ከፈልን ለማስገንባት ወሰንን። እከፋፈሉም የሚስማማንና የምንችለውም ነበር። እንዲህ አቅደን እያለ ጡረታ ለመውጣት እያኮበኮበ ያለ ወዳጃችን ተሰፋጽዮን ደለለው ወደ አዲስ አበባ መጥቶ እኛ ቤት አረፈ፤ እርሱም ጎረቤታችን እንዲሆን ሃሳብ አቅርቤለት ነበር፡፡

ወደ አገር ቤት ሲመጣ መኖሪያው ወደእዚያው እንደሚሄድ ስለማውቅ እሁድ ጠዋት ስአምልኮ የትኛው የመሠረተ ክርስቶስ አጥቢያ እንድሚሄድ ስጠይቀው

እንተስ አለኝ፡፡ ወደፊት አጥቢያችን ወደ ምትሆነው ወደ ካራ እንሂድ አልኩት። ያኔ እኔም ገና ወደዚያ ሄጄ አላውቅም ነበር፡፡ በካራ የመሰረተ ክርስቶስ አጥቢያ መኖሯን ብቻ ነበር የማውቀው፡፡ ተያይዘን ምናልባት አጥቢያችን ትሆናለች ወደአልናት ካራ ሄድን፡፡ እንደደርሰን አስተናጋጆች ወደፊት ጥሩ ቦታ ሰጡንና ተቀመጥን፡፡

ቋሚው አገልጋይዋ አልነበረም፤ ከውጭ ከሌላ ቤተ ክርስቲያን የተጋበዘ አገልጋይ ነበር፡፡ ሲሰብክ አስባበኩ ግራ ይገባል፣ የሚናገረው እራምባና ቆምቦ ይረግጣል። እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ የሚለውን ደግሞ በቃሉ ስንመረምረው ብዙ ጥያቄ ያስበት ነበር፡፡ ከአንድ ሰአት በላይ ከለፈለፈ በኋላ የጸሎት ፕሮግራም አካሂዳለሁ ብሎ ሰዎች ወደ ፊት እየመጡ ጸለየላቸው፡፡ እንዲት እህት ወደ ፊት እንድትማጣ ጋበዛት፤ መጣች አፈታችን ወደቀች፤ ወደ እርሷ መጥቶ እርኩስ መንፈሱን ሊያስወጣ ብዙ ነገር አለ፤ ተዘርራ እያለ ጎንበስ ብሎ እፍ እፍ ይልባት ጀመር፡፡ ለብኩቱም የጸሎት ፕሮግራሙም አልተዋጠልንም ነበር። ልንወጣ ስንል ተሰፋን "እስቲ ሽማግሌዎቹን እናናግር" ብለው አልታየውም፡፡

ቢሆንም ወደ መኪናችን ቀረብ ስንል አንድ ጠና ያለ ሰው ጠጋ ብሎ እንኳን ደህና መጣችሁ፣ እውቅሃለሁ አለኝ፡፡ የት ብዬ ስጠይቀው፡ ዱሮ በሌ (ኦሊምፒያ በምትባለው) ያመልክ እንደነበር ነገረኝ፡፡ አገልጋዩ ማነው? ስለው ስሙን ነገረኝ። በቤተ ክርስቲያናችን ከሚሰጡት ስልጠናዎች፣ ያአንድ አመት ለክርስቶስ ስልጠና ወይም በኮሌጃችን ከሚስጡት የሰርቲፊኬት ወይም የዲፕሎም ፕሮግራሞች ተከታትሎአል ወይ? አልኩት፡፡ የተከታተል አይመስለኝም አለኝ። በሳምንቱ መሃል ከአ.አ. ከልል ቢሮ ተደውሎ ባለፈው እሁድ የት አጥቢያ ነበርህ? አለኝ፤ ካራ ነበርሁ፤ ምነው አልኩት፤ የካራው አገልጋይ ደውሎ "የምን ሰላዮች ነው የላካችሁብን?" እንዳለው እና ያ አገልጋይ እያስቸገረ እንደሆነም ነገረኝ። ከወራት በኋላ ይሄው አገልጋይ፡ አንድ እሁድ ጠዋት ከዛሬ ጀምሮ ይህ ቤተ ክርስቲያን የመሠረተ ክርስቶስ አጥቢያ አይደለችም በማለት አጥቢያዋን ገነጠለ።





ለገጣፎ ከገባሁ በኋላ አንድ ቀን ከክልል ተደውሎ "የካራ አጥቢያን ነገም ቢገነጥልም በወሰደው እርምጃ ያልተሰማሙ ምእመናን መጀመሪያ በአንድ ቤተሰብ ቤት እየተሰበሰቡ በማምለክ አሁን በክልሉ እርዳታ አንድ ግቢ ተከራይተው መጠለያ ሠርተው ማምለክ ጀምረዋል፤ እርዳታ ያስፈልጋቸዋል" አለኝ፡፡ መልካም ብዬ ጊዜያዊ ሽማግሌዎችን ሰምክር መርዳት ጀመርኩ፡፡ ይህቺን አጥቢያም እንደ አጥቢያዬ መቁጠር ጀመርሁ፡፡ ከጊዜ በኋላ የልማት ኮሚቴ አባልም አደረጉኝ። ቦታ ገዝተን ጸሎት ቤት ልንሠራ ይገባል ብዬአቸው የገንዘብ አሰባሳቢ ኮሚቴ ሊቀ መንበር አድርገውኝ ከብዙ ሙከራ በኋላ ቦታ ገዛን፡፡ ጥሩ መጠለያም ሠራን፤ አላማችን ጸሎት ቤት መስራት ነበር። ቀጥለውበታል፡፡

በቤተክርስቲያናችንም የመሠረት ክርስቶሰ ኮሌጅ ቦርድ አባል በመሆን የደብረዘይቱ ቦታ እስከሚገዛበት ጊዜ አገልግያለሁ፡፡ የመጀመሪያው የቦርድ ሊቀ መንበርም ሆኜ ካገለገልሁ በኋላ ያን የመሪነት ቦታ ለዶክተር ከተማ በሰጠ በደስታ አስረከቤ ነበር። ከተማ ያን ቦርድ ለሁለት አመት ያህል ከመራ በሁዋላ የእኔም የአገልግሎት ዘመን በማለቁ ከቦርድ ወጣሁ፡፡ ከተማ እያገለገለ እያለ ኮሌጁ ሲቋቋም ያወጣነው የኮሌጁ ማስተዳደሪያ ደንብ ተለውጦ ከተማም የቦርድ ሊቀመንበር መሆኑ ብቻ ሳይሆን ከናዝሬት ወደ ሐረማያ በመመለሱ ከቦርዱም ወጣ፡፡ የኮሌጁ ቦርድ አባላት አመራረጥም ተለወጠ፡፡ ለውጡ በኮሊጁ አስተዳዳሪም ዘንድ ተቀባይነት አልነበረውም፡፡ ይህን ተከትሎ በቤተክርስቲያናችን ትልቅ ውዝግብ ተነስቶ ነበር። ውዝግቡ ባለመቀጠሉ እግዚአብሔር ይመስገን።

# ምዕራፍ 12

# ሌሎች አበይት ተሳትፎዎች

## በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ኅብረት

ከናይሮቢ እንድተመለስሁ ከመሠረተ ክርስቶስ ውጭ ያገኘሁት የመጀመሪያው የአገልግሎት እድል ከወዳጄና ጓደኛዬ ከማሞ ገብረ መስቀል ጋር በቢሊግርሃም የአለም አቀፍ የሳታላይት አገልግሎት አስተባባሪነት ነበር፡፡ ይህ ፕሮግራም መላውን የአዲስ አበባ አብያት ክርስቲያናት ያገናኘ ነበር፡፡ እኚህ ታላቅ የጌታ የወንጌል ሰባኪ በመላው አለም እየተዘዋወሩ በየታላላቅ አዳራሾችና ስቴዲየሞች ለብዙ ሺህ ሰዎች ወንጌልን ሰብከዋል፡፡ እንደመጨረሻ አገልግሎት ብለው ለመላው አለም በሳታላይት ወንጌል ለማጸራጨት ወሰኑ፡፡ የሳተላይት ተግባቦት መጀመሩ ነበር፡፡ በተጨማሪ በዚያው ጊዜ በልዩ ልዩ የታወቁ ለባኪዎች የቀረበ የክርስቲያን አገልጋዮች ኮርሰም ነበር። ከፖርቶሪኮ ስታዲዩም የሚያስተላለፉት መልእከት በሳተላይት መልእከት በቪዲዮ ከተቀረጸ በኋላ በየታላላቅ ከተሞች ስታዲየሞች ተላለፈ፡፡ ሕዝቡ በአዲስ አበባ ስታዲይም መልእከታቸውን በታላቅ ማሳያ (ስክሪን) ተመለከተ። በ1952 ዓ.ም በአካል በሰበኩበት ሲታዲዩም በዚህ መልክ ሰበኩ ማለት ነው። ይህ በአስመራም ታየ፡፡ በዚያም እንዲታይ ማቀነባበርና ማስተባበር የኔ ሥራ ስለነበር ዳግም ወደ አስመራ የመሄድ እድል ገጥሞኝ ነበር።

ወደ እዚያ መሄዴ በዚያን ጊዜ የህዝቡን ስሜትና አስተያየት ለመገንዘብ እድል ሰጥቶኝ ነበር፡፡ የጦርነት መንፈስ በመቆሙ ህዝቡ ተደስቶ ነበር። የሚቀጥለውን ስርአት በጉጉትና ተስፋ ይጠባበቅ ነበር። የኤርትራ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች ወንጌላውያን አብያት ክርስቲያናት ጋር ያላትን ግንኙነት





ለመገንዘብም ችያለሁ። ሊገባኝ ባልቻለ ሁኔታ በዚያ ፕሮግራም ለመተባበር ፈቃደኛ አልነበረችም። ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ በመሄድ ለመረዳት ፈልጌ ነበር። ስደርስ ዋና ጸሐፊዋ ናይሮቢ የማውቀው አቶ ዘሪት ነበር፡፡ እርሱን እንዳናግር ተነግሮኝ ላገኘው ግን አልቻልሁም ነበር። ወደ አዲስ አበባ ስመለስ አይሮፕላን ማረፊያ ሰው ሊሸኝ መጥቶ አገኘሁትና "ለምን አትተባበሩም" ብዬ ጠየቅኹት፤ "የቢሊግርሃሙ ፕሮግራም ሰዎች ጌታን እንዲቀበሉ የሚጠይቅ በመሆኑ "እኛ በአልተር ኮል (Alter call) አናምንም ስለዚህ ነው" አለኝ፡፡ "እንዴት አታምኑም ብዬም ለመወያየት ሞከርሁ" በጣም ገረመኝ። ከጊዜ በኋላ የኢሳይያስ መንግሥት ሌሎች ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትን ሕገ ወጥ ሲያደርግ የኤርትራ ወንጌላዊት መትረፏን ስረዳ ነበር ጉዳዩ የገባኝ።

## የእርቅና ሰላም ኮሚሽን

በቤተ ክርስቲያኔ እንዳሰብኩትና እንደ ተመኘሁት መጠን የመስበክ እድል ባይገጥመኝም በልዩ ልዩ ቦርዶችና ኮሚቴዎች ለማገልገል ያገኘሁት እድል ግን ብዙ ነበር። ከእነዚህ አንዱ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ሕብረት የእርቅና ሰላም ኮሚሽን ነው። አንዱ ተግባራችን የተከፈለቿውን የመጥምቃውያን ቤተ ክርስቲያን ማስታረቅ ነበር። ይህም ብዙ ጊዜ ወስዶብን ሳይሳካልን ቀርቷል። በዚያን ወቅት አንድ የሰማሁትን የሚገርመኝ አባባል ነበረ። እሱም በአንድ ክርስቲያንና አለማዊ መካከክል የተደረገ ወይይት ነው፤ በአጭሩ እንደሚከተለው ልግለጸው፡-

ክርስቲያን፡- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው፤

አለማዊው፡- እግዚአብሄር ሊያደርግ የማይችለው አለ፤

ክርስቲያን፡- እግዚአብሔር ሊያደርግ የማይችለው የለም፤

ዓለማዊው፡- የማይችለው አለ

ክርስቲያን፡- ምን የማይችለው ነገር አለ?

ዓለማዊው፡- ሁለት ጴንጤዎች ቢጣሉ ሊያስታርቅ አይችልም።

ይህ ነገር የፈጠራ ቢሆንም እውነት ሆኖ በማግኘቴ ቤተ ክርስቲያኖች ሲጣሉ በምናስታርቅበት ጊዜ ሁሉ ደጋግሜ ብዬዋለሁ። ጉዳዩ የእግዚአብሔር አለመቻል አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ነጻ ፈቃድ ሰለ ሰጠ ማንንም አያስገድድም፡፡ በመሆኑም ለመታረቅ ፈቃደኞች ባለ መሆናቸው አልታረቁም። እንደ ተለያዩ አሉ፤ ባለ መታረቃቸው ምክንያት ቄራ አካባቢ ያለው ጸሎት ቤት አሁንም በመንግሥት እጅ ነው።

ለኢትዮጵያ ወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያን ኅብረት እጅግ በጣም አሳዛኙና አሳፋሪው ነገር የቤተ እምነቶች የእርስ በእርስ ግጭትና መከፋፈል ነበር። ይህ ጎልቶ የታየው በሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተክርስቲያን የአዲስ አበባ አጥቢያና ከአዲስ አበባ ዉጭ ባሉት አጥቢያዎች በተፈጠረው አለመግባባትም ነበር። የእነርሱንም ሆነ የሌሎችን አለመግባባት ምክንያት መዘርዘር በእኔ ታሪክ ዉስጥ ቦታው ሰላልሆነ አልሞከረውም፡፡

ኮሚሽኑ የሁለቱን ወገን አለመግባባት ለማስታረቅ ብዙ ጣረ፤ ሳይሆንልን ቀረ። አባላቱ ብቻ ሳይሆኑ በመላው ዓለም ያሉ ክርስቲያኖች ጸለዩ፤ እግዚአብሔር የህዝቡን ጸሎት ሰማ፤ በብዙ ድርድር እርቅ ወረደ፤ ሃሌ ሉያ ብለናል፡፡

ሊላይቱ የተከፍላ የነበረች ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ የሱስ ነበረች፤ የእርሱዋም ችግር በመንግስት ደረጃ ሳይቀር የተተቸና ለአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ታላቅ ሃዘንና ሐፍረትም ነበር፡፡ የእነርሱም መከፈል ተጨማሪ ለወንጌል ሰርጭት እንቅፋት ነበር። እርሷን ለማስታረቅ ከኢትዮጵያ እኛ ብቻ ሳንሆን ከውጪ በተለይ በእስካዲኔቪያ ያሉት አጋሮቻቸው ጭምር ነበሩበት፡፡ የዉጭው ሊያስማማቸው አልቻለም፡፡ እግዚአብሔር ከቤተክርስቲያኒቷ አስታራቂዎች አስነሳና አስታረቃቸው፤ ሃሊ ሉያ።





## የወርልድ ቪዥን አማካሪ ቦርድ አባልነት

የኢትዮጵያው ወርልድ ቪዥን በሌሎች አገሮች ካሉት ፕሮግራሞች ትልቁ ይመስለኛል፡፡ ለዚህም ያበቃው ያ በአለም ደረጃ ሁልጊዜ ደሃና ረሃብተኞች ሆነን እንድንታይ ያደረገን የ1977ቱ ከስተት ሳይሆን አይቀርም፡፡ በዚያን ጊዜ ብዙ ሠራተኞች አስልፎ ሰለ ነበር ድርቁ መጨረሻ ላይ ሰራተኞችን መቀነስ ነበረበት፡፡ ይህ ሃላፊነት የወደቀው በአብሮ አደጌ ጸጋ ወልደ ማርያም ላይ ነበር፡፡

ጸጋ ደፋርና ቆራጥ ሰው ነው፤ ሥራውን እንደ ጀመረ ያደረገው ለውጥ የድርቁን ጊዜ የዘመቻ መምሪያ ከኢትዮጵያ ሆቴል አውጥቶ አንድ መጠለያ አሰርቶ ወደ እዚያ እንዲሄድ ማድረግ ነበር፡፡ ሌላው አስቸጋሪ ሥራ ሠራተኞች መቀነስ ነበር፡፡ መደበኛውን ሥራ የሚመራው አቶ ሰሎሞን ሉሉ ሲሆን የድርቁን ሥራ የሚመራው ኬን ትሬሲ የሚባል አውስትራላዊ ሰው ነበር። ዶክተር ተሰፋ ጽዮንም ናይሮቢ ሆኖ ይረዳ ሰለ ነበር ጸጋ ጡረታ መውጣቱን ሲሰማ ወርልድ ቪዥን እንዲገባ ጋበዘው፡፡ የወርልድ ቪዥን የድርቅ ፕሮግራምም ወደ ልማት እንዲዞር እየታሰበም ነበር፡፡ አብሮ አደጌ ጸጋ ይህን ጉዳይ በደሰታ በማየቱ ግብዣውን ተቀበለ።

ጸጋ ወርልድ ቪዥንን ከነበረችበት ችግር ዉስጥ ማውጣት ብቻ ሳይሆን ቢሮም ያስገነባላት ሰው ነው። እርሱ ለምስራቅ አፍሪቃ ወርልድ ቪዥን ዲሬክተር ለመሆን ወደ ናይሮቢ ሲሄድ እኔ ናይሮቢን ለቅቄ ወደ አዲስ አበባ መጥቼያለሁ። ዝርዝሩን ባላውቅም የኢትዮጵያው ወርልድ ቪዥን ቦርድ የተቋቋመው ያኔ ነበር።

የኢትዮጵያውን ወርልድ ቪዥን የተረከበው አዲሱ ዳይሬክተር አቶ ሙሉጌታ አበበ ለወርልድ ቪዥን ቦርድ አባልነት ጠይቀኝ፡፡ “ጋሼ ጸጋ የኢትዮጵያ ወርልድ ቪዥን ቦርድ አባል እንድትሆን ጠቁሞሃል” አለኝ። ከላይ ያለውን ምናልባት የዘረዘርኩት እንዴት የዚህ ድርጅት አማካሪ ቦርድ አባል እንደሆንሁ ለመግለጽ ነው። የዚህ ድርጅት የአማካሪ ቦርድ አባል በመሆኔ ይህን ፊጽሜያለሁ ባልልም ከሌሎች አባላት ጋር ለዚህ ታላቅ ድርጅት ብዙ ጠቃሚ ምክሮችን

ለግሰናል። የኢትዮጵያው ወርልድ ቪዥን ፈረንጆች ሠራተኞች የሌለው በመሆኑ የሚያመመሰግኑትና የሚተቹትም እንዳሉ የሰማሁት ያኔ ነበር። ለቦርዱም መተዳደሪያና መመሪያ ያወጣነው ያኔ ነው። ካወጣነው ደንብ አንዱ የቦርድ አባልነት የእድሜ ልክ በመሆን ፈንታ ለተወሰነ አመት እንዲሆን የሚል ስለነበረ የተወሰነ አመት አገልግዬ የወርቅ ሃብል ተሸልሜ አባልነቴ አበቃ፡፡ እኔ ከሰጠሁት ያገኘሁት ይበልጣል፤ ስለዚህም አምላኪን አመሰግናለሁ።

## የተስፋ ድርጅት

የዚህ ድርጅት መስራች አሜሪካዊው ሚሲዮናዊ ሚስተር ጃክ ስሚዝ ነው። ድርጀቱን መጀመሪያ ሲያቋቁም እኔ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ዋና ጸሃፊ ነበርኩ፡፡ አራት ኪሎ ያለው ህንጻችን አንደ ገባን ከቢሮዬ ጎን ያለች አንዲት ቢሮ ለጥቼው እዚያች ዉስጥ ሆኖ ያቋቋመው ድርጅት ነው። የጎዳና ተዳዳሪዎችን ለመርዳት እንዳቀደ ነግሮኝ ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ተነጋገርን። ለሙከራም አንዲት ቤት ጉለሌ ተከራይቶ ጥቂት የአናጢ መሳሪያዎች ገዝቶ ልጆቹን ያሠራቸው ነበር። ለዚህ ዓላማው ድርጀት ሲያቋቁም እንዳለበ ነግሮኝ፣ መተዳደሪያ ደንብ አርቅቀን ድርጅቱን በመንግሰት ዘንድ አሰመዘገብን። እኔ ከመስራች አባሎች አንዱና የመጀመሪያውም ቦርድ ሰብሳቢም ነበርሁ።

በመጀመሪያዎቹ አመታት ጃክ ያንከራተተኝ ለድርጅቱ ቤት መሥሪያ ቦታ በመፈለግና፤ ቦታም ሲያገኝ ከባለቤቶቹ ጋር በመነጋገር ነበር፡፡ በዚያን ዘመን ቦታ ለመግዛት ያለው ጣጣ ብዙ ነበር። ሺያጩ መሬቱ የርሱ ለመሆኑ ማረጋገጥ፣ ዋጋ መከራከር ወዘተ የሚባሉ ዝርዝር ስራዎች ነበሩበት። አንድ በጣም የወደድነው ቦታ አቃቂ መንገድ ላይ አሁን ሲ. ር. ዲ ኤ. ያስራበት ቦታ አለፍ ብሎ ያለ ያንዲት ልእልት ቦታ ነበረ፡፡ ይህች ቦታ ጥሩ ነች ብለን ተንበርክክን ጸልየንባት ነበር።

ሌላው ያየነው አየር ጤና ያለው አሁን የተስፋ ድርጅት ት/ቤት የተሠራበት





ቦታ ነው። በሙሉ ሳይሆን በከፊል። ይህን ቦታ ለመግዛት እየተነጋገርን እያለ የመንግስት ለውጥ መጣ። እኔም ወደ ናይሮቢ ሄድሁ፤ መሬት መግዛትና መለወጥም ቆመ። ጃክ የሚረዳው ፈልጎ ባህርዳር ወሰጄ በፖሊቴክኒክ ያስለጠንኩት ከካሳ አጋፋሪ ጋር አገናኘሁት፡፡ ካሳ በፖሊቴክኒክ ኢኒስቲትዩት የኤሌትሪክ ቴክኖሎጂ ተምርቆ መጀመሪያ ቆቃ ይሠራ ነበረ ከዚያ ወጥቶ የድኩማን ድርጅት ሃላፊ ሆኖ ነበር። ያም ቦታ ተስፋፍቶ ተሰጠውና ትምህርት ቤቱን፣ ወርክ ሾፖች፣ እንደ አቾሎኒ ቅቤ ያለ ምግብ ማዘጋጃ ቤት አሰርተው፣ የልጆች መኖሪያም ቤት ሠሩ፤ የዶሮ ማርቢያም ሠርተው ዶሮም ማርባት ጀመሩ። ሥራው እንዲህ እያለ ቀጠለ፤ ካሳም አስር አመት ያህል ካገለገለ በኋላ ሙሉ ጊዜውን ለቤተ ክርስቲያን ለመስጠት ወሰነ፡፡ ጃክ ስሚዝ የአገልግሰት ፍላጎት ያለውን ዶክተር ሚናስ ብሩክን በማግኘቱ አዲስ አለቃ አደረገው፤ ሚናስ የደሴ ልጅ በመሆኑ በአካባቢው ካለው ችግር የተነሳ እዚያም ሌላ ቅርንጫፍ ከፈተ።

ከናይሮቢ ስመለስ ጃክ ስሚዝ ወደ ቦርድ አባልነት እንድመለስ ስለ ጠየቀኝ አንደገና የተስፋ ድርጅት የቦርድ አባል ሆንሁ። ብዙም ሳልቆይ የቀድሞው ሰብሳቢ አቶ መኩሪያ ጅማ እድሜ ልኬን ሰብሳቢ ልሆን አይገባም በማለታቸው ሰብሳቢ ሆንሁ። የቦርድ አባል ሆኜ ይህን ሠራሁ፤ ያን አስፈጸምኩ ማለት አይቻልም። የሚሠራው በቡድን ነውና፤ ቢሆንም በቦርድ ዉስጥ ሆኜ ተቀባይነት ያገኙ ያቀረብኳቸው ወሳኝ ነገሮች ነበሩ፡፡ ዶክተር ዓለሙ ገብረወልድ፣ አቶ ነጋሽ ከበደና ዶክተር ጥላሁን አበራ ፋንታ የቦርድ አባል እንዲሆኑ የጠቆምኩ እኔ ነበርኩ። አንዱ ያሳሰበኝ እኔ የቦርድ አባል የሆንሁበት አኳኋንና ሌሎችም የቦርድ አባል እያደረግን ያለንበት ዘዴ ነበር፡፡ የቦርድ አባል የሚኮነው በመስራቹ ምርጫ ነበር፡፡ ዘዴው በተለይ አሜሪካ በቤተክርስቲያን ሳይቀር በሰፊው ይሠራበታል። ይህ ሊቀጥል እንደማይገባ በመግለጽ የኢትዮጵያ መንግስትም በሚፈልገው መሠረት መተዳደሪያ ህግ አወጣን፡፡ በሀት የቦርድ አባል አገልግሎት ዘመን መወሰንና አመራረጥም አስገባን። የቦርድ አባልን የሚመርጥ አካል ያስፈልጋል አልኩ፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ማህበር የቦርድ አባል የሚኮነው በአባላት ምርጫ ነው፡፡ የተስፋ ድርጅት አባላት የሉትም፤ ኬንያ ሆኜ የናይሮቢ ግራጁዌት ስኩል ኦፍ ቲዎሎጂ ባለአደራ ነበርሁ፡፡ በመሆኔም የዚህ ተቋም ባለቤት ነበርሁ። ባላደራ ሆኜ የተመረጥሁት በማንነቴና የቤተክርስቲያን አገልጋዮችን ለማሰልጠን ታላቅ ናፍቆት ያለኝ ሰው መሆኔ ስለሚታወቅ ነበር፡፡

እኛ ባላደራዎች በአመት አንዴ እንሰበሰባለን፡፡ ትምህርት ቤቱን የሚመሩ እንመርጣለን፡፡ ስለ ት/ቤቱ ሂደትና የሂሳብ ሪፖርት ይቀርብልናል፤ ለሚቀጥለው አመት በጀት እናጸድቃለን፡፡ ሌላም ከፍተኛ ጉድይ ካለ የታሰበውን ለምተን፥ተወያይተን እናጸድቃለን። ይህቼን አሠራር የተስፋ ድርጅት እንዲከተል ሃሳብ አቀርብሁ። ይህም ሃሳብ በመተዳደሪያ ደንቡ እንዲካተት በማድረግ ባላደራ አባላት መረጥንና የአመታዊ ጠቅላላ ሰብሰባ አባላት አልናቸው።

እነኚህ ባለአደራ አባላት በአመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባሉ፤ ሪፖርት ይሰማሉ፡፡ ከመረጡት የሂሳብ መርማሪ የሂሳብ ሪፖርት ይቀርብላቸዋል። የቦርድ አባላት ይመርጣሉ፤ ቦርዱ የሚጠቁመውን ሰው የተስፋ ድርጅት ዋና ሃላፊ ይሾማሉ። መስራቹ ጃክ ስሚዝ በህይወት የለም። ቢሆንም ሥራው እርሱ ከነበረበት አኳኋን በተሻለ፣ በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በደሴ፣ በጋምቤላና በሸምጥ ሸለቆ ዉስጥ፣ በሁለት ከተሞች ተጨማሪ ፕሮግራሞች አሉት። ታላቅ ዩኒቨርሲቲም ተቋቁሞ እየተካሄደ ነው። የተስፋ ድርጅት እየሠራ ያለውንና እንዴት እየተካሄደ እንዳለ ሳይ በጣም ደስ ይለኛል፡፡ በዚህ ድርጅት እድገት በነበረኝ ተሳትፎ አምላኬን አመሰግናለሁ።

## የአፍሪቃ ኢቫንጀሊካል ኢንተርፕራይዝ ቦርድ

የAEE-E (Africa Evangelistic Enterprise – Ethiopia) ቦርድ አባል የሆንኩት በአቶ ብርሃኑ ደረሰ ጥያቄ መሠረት ነው፡፡ ኤ.ኢ.ኢ.- ኢትዮጵያን ወደ አገራችን ያመጣው እርሱ ነው። ወንድም ብርሃኑ ቀድሞ በበሥራተ ወንጌል ዉስጥ የድርጅቱ ሂሳብ ሰራተኛ ነበር፤ እዛ እያለ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ አሜሪካ ተላከ፡፡ ከዚያ ከተመለሰ በኋላ NIST (Nairobi International School of Theology) በሚባለው በማስተርስ ደረጃ ተመርቆ ኖርዊጂያን ኢይድ ለጥቂት ጊዜ ሰራ፡፡ ከዚያ በኋላ ናይሮቢ ያለው የኤ.ኢ.ኢ. መስሪያ ቤት ችግር ስለነበረው ይህን መሥሪያ ቤት እንዲረዳ ተጠይቆ እየሠራ በነበረበት ወቅት የልቡ ትርታ የወንጌል ስርጭት በመሆኑ የዚህ ደርጅት የአፍሪቃው ቡድን አባል በመሆን ማገልገል ጀመረ።

የድርጅቱ አላማ "የአፍሪካ ከተሞችን በቃልና በተግባር በወንጌል መድረስ" የሚል በመሆኑ በአዲስ አበባ በጃን ሜዳና በስታዲዮም ታላቅ የጅማ ስብከት ወንጌል እንዲካሄድ አድርጓል። የአፍሪካ ኢንተርፕራይስን ን የጀመረው ማይክል ካሰዲ የሚባል በደቡብ አፍሪቃ የሚኖር እንግሊዛዊ ታላቅ ወንጌላዊ ነው፡፡ በኋላ ቢሾፕ ፌስቶ ኪቬንጌሪ የሚባለው ታላቁ የዩጋንዳ ወንጌላዊ ኢቫንጀሊስቲክ የሚለውን ቃል አስጨምሮ ተባባሪ ሆነ። ድርጅቱ በአውስትራሊያ፣ ኒው ዚላንድ፣ እንግሊዝ አገር፣ አሜሪካና ካናዳ ደጋፊ ድርጅቶች አሉት። በአፍሪቃ ዉስጥ በጋና፥ ዛይር፥ ሩዋንድ፣ ዩጋንዳ፣ ኬንያ፣ ታንዛኒያ፣ ማላዊ፣ ዚምባብዌና ደቡብ አፍሪቃ ቅርንጫፍ ቢሮዎች አሉት፡፡ ብርሃኑ ከቡድኑ ሲቀላቀል፥ ናይሮቢ ሆኖ ጊዜውም የደርግ ዘመን በመሆኑ በዚያው የኢትዮጵያ ቢሮ ከፈተና የአዲስ አበባውን የጅማ ስብከተ ወንጌል አካሄደ። ደርግ ከተገረሰሰ በኋላ ቢሮውን ወደ አዲስ አበባ አመጣ። በሌላው አገር ያሉት ቢሮዎች የሚመሩት በቦርድ ስለሆነ እርሱም ቦርድ ስለሚያስፈልገው እኔንና ሌሎችን መልምሎ እኔ የቦርዱ ሰብሳቢ ነህ ብሎ አብረን ማገልገል ቀጠልን። በዚህ መልክ ለሰባት ዓመታት ያህል ከሰራን በኋላ ሥራውን ለኛ አስረከቦ ወደ አሜርካ ተዛወረ።

የኤ.ኢ.ኢም ቦርድ አባላት መዳቢው የድርጅቱ ሃላፊ ሊሆን አይገባውም በማለት በተስፋ ድርጅት እንዳደረግሁት የባለአደራዎች ሥርአት አስጀምሬ ሰብሳቢነቱን ለሌላ የቦርድ አባል (ኃይሉ ወልደሰማያት) አስረከቢ ወደ አሜሪካ ሄድሁ። ስሙን የኢትዮጵያ ለማስመሰል እንዲቀየር ምክሬ ሳይሳካልኝ ቀረ።

## ክርስትናና ፖለቲካ

ከአቶ ብርሃኑ ደረሰ ጋር በምናገለግልበት ጊዜ፣ ብርሃኑ በሐዋሳ ሰመሪዎች ባዘጋጀው ስብሰባ ላይ ስለ መንግሥት፣ ስለ ፍትህና እርቅ ጉዳይ ንግግር እንዳደርግ ጠየቀኝ:: ስለዚህ ምን እውቃለሁና ነው ይህን የምትጠይቀኝ ብለው አጥንተህ ተመራምረህ ጥናቱን ማቅረብ አለብህ አለኝ:: ለዚህ እንዲረዳኝ አንድ ደቡብ አፍሪቃዊ ክርስቲያን ፖለቲከኛ ያደረገውን በካሴት የተቀረጸውን አንድሰማ ሰጠኝ:: ያ ክርስቲያን ፖለቲከኛ ካላቸው ነገሮች ውስጥ ልቤን የነካውና እንዳስብም ያደረገኝ፣ "ፖለቲካ ቆሻሻ አይደለም ያቆሸሹት ፖለቲከኞች ናቸው" ("POLETICS IS NOT DIRTY. WHAT MADE IT DIRTY ARE POLETICIAN") የሚለው ነበር።

ክርስትናና ፖለቲካ ዙሪያ ማጥናት ጀመርሁ። በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ የሳኦል፣ ዳዊት፣ ሰሎሞን፣ ዮሴፍ፣ ዳንኤል፣ አስቴር ሥራ በአሁኑ አስተሳሰብና አጠራር የፖለቲከኞች ሥራ መሆኑን፣ የፖለቲካ ሥራ ህዝብን መምራትና ማገልገል መሆኑን፣ እንዲሁም አገሪቱ የምትመራበትን ሕግ (ህገ መንግሥት) ማዉጣት መሆኑን ተረዳሁ:: በየጊዜው የሚወጣው ነጋሪት ጋዜጣ የሚባለው የሚወጣው በእነርሱ ነው::

ከዚህም በላይ ጌታ ኢየሱስ የዐለም ጨው ናችሁ፤ . . የዐለም ብርሃን ናችሁ ብሏል፤ ክርስቲያን ጨው ሆኖ ህብረተሰብን ሊያጣፍጥ የሚችለው ወይም ከመበስበስ የሚጠብቀው ዉስጥ በመግባት ነው እንጂ ዉጭ ሆኖ አይደለም አልሁኝ። ብርሃንም ሲሆን የሚችለው ጨለማው ዉስጥ ሆኖ ነው እንጂ ሰብቻው ቁጭ ብሎ አይደለም ብዬ አመንኩ። እስካዚያች ጊዜ ድረስ እኔም ክርስቲያን ፖለቲካ ዉስጥ መግባት የለበትም፣ ከፖለቲካ ርቆ መኖር አለበት ባይ ነበርሁ። የሕዝበ ክርስቲያኑ አቋምም ይሄው ነበር:: ይህ መለወጥ አለበት ብዬ ተነሳሁ። አሁንም አላሰሁ።

በታላቅ ፍራቻ ይህን ሃሳብ አደባበሬ ከመጽሐፍ ቅዱስ እየጠቀስሁ ጽሑፌን ለውይይት አቀረብሁ:: ከፍርሐቴ የተነሳ ቆሜ አልናገርም ብዬ ሳሎን ዉስጥ





ቁጭ ብለን እንደምንጨዋወት እስበ ብዬ ከፍ ባለው ቦታ ወንበር ላይ ቁጭ ብዬ ሃሳቤን አቀረብሁ። ከንግግሬ በኋላ መጀመሪያ የቀረበልኝ ጥያቄ፤-

"ጨው አባይ ወንዝ ቢፈነጠቅ የአባይ ወንዝ ይዞት ይሄዳል፤ አንድ ክርስቲያን ፖለቲካ ዉስጥ ሲገባም እንደዚሁ ነው" የሚል ነበር::

«የአለም ጨው ናችሁ ያለው ኢየሱስ ነው፤ ለዚህ ንፅፅር መልስ የለኝም፤ ኢየሱስን ጠይቀው» አልኩት::

### ሌላው ተነሳና:-

"አንድ ክርስቲያን ፖለቲካ ዉስጥ ሲገባ፣ እኛ የምናስበው እንደ ጥፋተኛ ነው። አንተ እንዳልከው ዳንኤል እንዳደርገው በጸሎት እንዲበረታ አናደርገውም፤ አንጸልይለትም፤ ስለ ምንኮንነው ከቤተ ክርስቲያን እንዲርቅ አናደርገዋለን" አለ።

በኢትዮጵያ ብዙ ወንጌላውያን ፖለቲከኞች የሚገኙት በደቡብ ክልል ስለ ሆነ ይህን አስተያየት በርካቶች ተቀባበሉት። (ያሁኑ ጠቅላይ ምኒስትራችን ከሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ከደቡብ መሆኑን ያስታዉሷል)፤ እንደ ፈራሁት አልነበረም። ንግግሬ እኔን ብቻ ሳይሆን የብዙዎችን አስተሳሰብ ሰወጠ:: ፖለቲካ ዉስጥ ያሉትን ሊያቀርቡ፣ ሊያደፋፍሩ በየፊናቸው ወስነው የሄዱ ይመስለኛል።

ይህን የጥናት ጽሁፌን አዲስ አበባ ላይ በአብያተ ክርስቲያናት ስብስባ ላይ ደግሜ እንዳቀርብ ጥያቄ ቀረበልኝ:: ክርስቲያን በምን በምን ደረጃና መንገድ በፖለቲካ ሊሳተፍ እንደሚገባው ሃሳብ አቀረብሁ።

በኅብረቱ ደረጃ ብዙ ተቀባይነት አገኘ ህብረቱም በጉዳዩ ገፍቶበት ወንጌላውያን ክርስቲያኖች በሚከተለው አገር አቀፍ ምርጫ እንዲሳተፉ ለማደፋፈር አንድ ግብረሀይል አቋቋሙ። እኔም እንደአስተባባሪ ሆኜ ተሾምሁ፤ ይህንንም በተመለከተ ወንጌላውያን ክርስቲያኖችን ያማከለ አጭር ጽሑፍ አዘጋጅቼ የሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎች ካስማመሩት በኋላ ወደ ሙቶ ሺህ ኮቢ ታትሞ ተሰራጨ።

ዋና ዓላማው ወንጌላውያን ክርስቲያናት በ1997 ዓ.ም ምርጫ በትጋት እንዲሳተፉ ለማበረታት ነበር።

***

እኔም እየዞርሁ ስልጠና ስሰጥ እንዲህማ ከሆነ አንተ ለምን ለምርጫ እራስህን አታቀርብም የሚል ጥያቄ ይቀርብልኝ ጀመር።

በአሰማችን ታላላቅ ሰውጦች እንዲመጡ ያደረጉ ክርስቲያን ፖለቲከኞች እንደ ሆኑ አውቃለሁ። ለምሣሌ ዊሊያም ዊልበርፎርስ የሚባለው የእንግሊዝ አገር የፓርላማ አባል የባርያ ንግድ እንዲቆም ለማድረግ ለ35 አመት ደግሞ ደጋግሞ ሕግ እንዲወጣ በመሟገቱ በመጨረሻ ተሳካለት። የአሜሪካ ሕገ መንግስት በመጽሐፍ ቅዱስ መርሆ (principle) ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ያደረጉት የመጀመሪያዎቹ የሕገ መንግሥቱ አርቃቂዎች ክርስቲያኖች ስለ ነበሩ ነው። በገንዘባቸው ላይ IN GOD WE TRUST የሚል ሊጻፍ የበቃው በክርስቲያን ፖለቲከኞች ምክንያት ነበር።

ከብዙ ሰዎች ጋር መከርሁ፤ አበረታቱኝ። እኔም የምሰብከውን መኖር አለብኝ የምል ሰው ነኝ። ለሰዎችም ምሳሌ ለመሆን ፈለግሁ። ለሃሳቡ አጄን ስሰጥ በየትኛው ፓርቲ? ልሣተፍ የሚለው ጥያቄ ቦግ አለብኝ። የማንም ፓርቲ አባል ላልሆን በግል ለመወዳደር ወሰንሁና የደጋፊዎች ፊርማ ማሰባሰብ ጀመርሁ።

የጀመርሁት በሰፈሬ ባሉት የክርስቲያኖች የእድር ስብሰባ ላይ ነበር። አላማዬን የምትገልጽ በአዲስ አበባ ወረዳ 17 ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ለመሆን ስለምፈልግ ድጋፋችሁን ስጡኝ የምትል ናት። በግል ለመወዳደር 1000 ፊርማ ያስፈልጋል። አንድ ቀን ማታ አንድ የማላውቀው ሰው ደወለና በግል ለመወዳደር በመግለጽ የበተንከው በእጄ አለ፤ 1000 ፊርማ አግኝተህ ብትወዳደር አትመረጥም፤ እንዳንተ ያሉ ብዙ ናቸው አለኝ። ያለው እውነት ነበር። የጀመርኩትን ለመቀጠል አንድ ፓርቲ ውስጥ መግባት አለብኝ ግን የትኛው ፓርቲ ዉስጥ ልግባ?





ስለእያንዳንዱ ፓርቲ የማውቀውን ደረደርሁ። መጀመሪያ የተመለከትሁት ኢህዴግን ነው። የኢህዴግን ፓርቲ ብመረጥ ከአራቱ አንዱ ዉስጥ መግባት አለብኝ ከኢህዴግ ፍልስፍና የማልቀበለውና የማልወደው የዘር ፖለቲካውን ነው። ዘርህ ምንድነው ብዬ ስጠይቅ የምመልሰው እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ በማለት ነው። ታዲያ ይህ አምብዛም አላስኬደኝም። ቀበሌዬ በሰጠኝ መታወቂያ ላይ፣ ብሄር - አማራ ይላል። አፍሬበት ሳይሆን ብሄሬ አማራ ነው ብዬ አላውቅም። ያም ሆነ ይህ በኢህዴግ ፓርቲ ዉስጥ አልሳተፍም አልሁ፤ የቀናኝ የህብረት ፓርቲና የቅንጅት ነበሩ።

አቶ ልደቱን ቢሮው ሄድሁና አነጋገርሁት። ዶክተር በየነ ጴጥሮስን ለምሳ ጋበዝሁትና ፖለቲካን እኛ ክርስቲያኖች እንደኮረንቲ የምናስበው ቢሆንም ፖለቲካ ውስጥ ለመግባት አያስብሁ መሆኔን ነገርሁት፤ የፓርቲዎች መብዛት ጥሩ እንዳልሆነ ሃሳቤን ገለጽሁለት። ሁለቱም የፓርቲዎቻቸው አባል ልደቱ በኢዴፓ በኩል የቅንጅት፣ ዶክተር በየነ የህብረት እንድሆን ጋበዙኝ።

ከቀናት በኋላ ወደ አቶ ልደቱ ሄድሁና በቅንጅት ስም ልሰልፍ አልኩት። የምፈልገውም በወረዳዬ ተወዳድሬ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለመግባት ነው አልኩት። "በወረዳ 17 ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሊወዳደር የተሰለፈው የፖለቲካ ልምድ ያለው ሰው ነው፤ በሌላ ወረዳ ብናሰልፍህስ" አለኝና አማረጠኝ፤ ላስብበት አልሁና ተለያየን። በመሃሉ ለኤ.ኢ.ኢ. ስብሰባ ወደ ደቡብ አፍሪቃ ሄድሁ። ስመለስ ግደይ፡ ልደቱ ደውሎልህ ነበር፤ ለምንድነው የሚፈልግህ? አለቺኝ።

በማግስቱ ለምን ፈለግከኝ አልኩት፤ የመመደቢያው ቀን ሳያልፍ ምርጫህን እንድትነግረኝ ነበር የደወልኩልህ። አሁንማ ተወሰነ ቢሆንም ከአሁን ቀደም እንዳልሁህ የአዲስ አበባ ክልል ምክር ቤትም ወሳኝ ነው አለኝ። አዲስ አበባን ማሸነፍ ለእኛ ትልቅ ነገር ነው፤ ስለዚህ በወረዳ 17 ለአዲስ አበባ ምክር ቤት ልመዝግብህ ብሎኝ በዚሁ ተስማምተን ተለያየን። እንዲሰው በኢዴፓ ስም በወረዳ 17 እንድወዳደር ለምርጫ ቦርድ ስሜን ሰጠ። አራቱ ፓርቲዎች

(ኢዴአፓ፣ መኢአድ፣ ኢድሲ፣ እና ቀስተ ደመና) ቅንጅት በሚል ስም እንዲወዳደሩ የምርጫ ቦርድ ስለ ፈቀደ በቅንጅት ስም ለአዲስ አበባ ምክር ቤት ለውድድር ቀረብሁ።

የ1997 ምርጫ ውድድር ነጻና እውነተኛ ውድድር ነበር:: በየአዳራሹና ባፍሪቃ አዳራሽ ሳይቀር የተደረጉት የውድድር ገለጻዎች፣ በሬዲዮና ቴሌቪዥን የቀረቡት መግለጫዎች ዲሞክራሲያዊ ነበሩ:: ምርጫው ሲደረግ አንድ ሳምንት ሲቀር በመስቀል አደባባይ ቅንጅት የድጋፍ ሰልፍ ጠራ:: ኢ.ህዴግም አንድ ቀን ቀደም ብሎ ለቅዳሜ ሰልፍ ጠራ:: የቅዳሜው የኢ.ህ.ዴ.ግ ታላቅ የመንግስት ድጋፍ የነበረው በመሆኑ በየቀበሌው የተደገፈ በመሆኑ ብዙ ህዝብ ወደ መስቀል አዳባባይ ጎረፈ:: ጠቅላይ ሚኒስትር መለስም አድርጎ የማያውቀውን በመስቀል አደባባይ በሕዝብ መሃል ተገኝቶ "ይህ የሕዝብ ማእበል ነው" አለ:: እንከን የለሽ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ተከሄዶ ኢ.ህ.ዴ.ግ. እንደሚያሸንፍ ገለጸ።

ማታ በቴሌቪዥን የተላለፈውን ላይ ምንም የማሸነፍ እድል የለንም ብዬ ገመትሁ። ቅንጅት ሰልፉን የጠራው ለእሁድ ከሰዓት በኋላ በስምንት ሰአት ጀምሮ ነበር። እኛ የፓርቲው አባላት ቀደም ብለን መገኘት ቢኖርብንም እኔ የእሁድ ጠዋት አምልኮዬን በምንም ምክንያት ላላስተጓጉል አቋም ስለነበረኝ ምስራቅ አ.አ. መሠረተ ክርስቶስ አምልኬ በሰባት ሰአት ገደማ ጉዞዬን ወደ መስቀል አደባባይ ቀጠልሁ:: ኡራኤል ቤተ ክርስቲያን ስደርስ ወደ ፊት እንዳልሄድ ተከለከልሁ፤ በፍል ውሃ በኩል አልፌ ወደ መስቀል አደባባይ ለመሄድ ፈለግሁ፤ አልቻልኩም። መኪናዬን ቴሌኮሙኒኬሽን ግቢ ለማቆም ብፈልግ አይቻልም ተባልሁ:: ጤና ጥበቃ ፊት ለፊት የማውቀው አንድ ጋራዥ አለ፤ ግቢውን አስከፍቼ እዚያ አቁሜ ወጣሁ:: በእግሬ ወደ አደባባዩ መሄድ ስጀምር ከመርካቶ አካባቢ ሰዎች ሆ! እያሉ በመጨፈር ወደ እዚያ ይጓዛሉ፤ ከነርሱ ጋር እየተጋፋሁ ስታዲዬም ስደርስ ከሰው ብዛት የተነሳ ወደ ፊት ለመሄድ ተሳነኝ:: እንደ ምንም ብዬ እየተጋፋሁ አደባባዩ መሐል ስደርስ ኤሌትሪክ ለለጠፉ በባትሪ ሃይል የድምጽ ማጉያውን ለማሠራት ሲሞክሩ አየኋቸው:: ይህ ይደርሳል ብለን ባለመዘጋጀታችን አዘንሁ::





ሰዎች ልደቱን በትከሻቸው ተሸክመው ሆ ሲሉ አየሁ:: ሌሎች "የንብ ቆዳ ፈላጊ፣ የንብ ቆዳ ፈላጊ" እያሉ ሲያሾፉ ሰማሁ። ያን ለት በአደባባዩ የሚያጠግብ መግለጫ አልተሰጠም ነበር። በማግስቱ በፎቶግራፍ እንዳየሁት በኤርፖርት መንገድ በኩል የነበረው ህዝብ መጨረሻው እስከ የት እንደ ነበረ ማየት አይቻልም ነበር:: በናዝሬት መንገድ መሿለኪያ ሕንፃዎች ላይ ተንጠልጥሏል:: በወዲህ እስከ ባቡር ጣቢያ ተጨናንቋል፤ የቅዳሜው የሕዝብ ማእበል ከተባለ ለዛሬው ግን መግለጫ ቃል የለውም። ቢ.ቢ.ሲ. ሲዘግብ "ይሄን ያህል ሰው የታየበት ቀን በታሪክ በእስም የለም ... ጥቂት የሚቀረበው በሮም ጳጳሱ የሞቱ ጊዜ የወጣው ህዝብ ነው" አለ። በታላቅ ደስታ ወደ ቤቴ ተመለስሁ። በዚያን ዕለት ያን ያህል ህዝብ ተሰብስቦ ምንም አይነት ችግር አልተከሰተም ነበር።

***

ምርጫው ተካሄደ፤ ቅንጅት በተለይ አዲስ አበባን ማሸነፉ ግልፁ ሆነ:: የፓርቲአችን ሃላፊዎች ስለ አጠቃላዩ ዉጤት ምን እናድርግ እያሉ ሲነታረኩ እኔ ቅንጅት አዲስ አበባን ማሸነፉ በጣም ያሳሰበኝ ጀምሯል:: አዲስ አበባን የማስተዳደር ጉዳይ በእኔና በብጤዎቼ ላይ ሊወድቅ ነው ማለት ነው:: ይህ ምን ማለት ነው? ከተማን ስለማስተዳደር እኔም ሆንሁ ሌሎች ምን እናውቃለን?። በዚያን ሰሞን ለኤ. ኤ. ኤ. ስብሰባ ወደ ናይሮቢ ሄጄ ስለ ነበር ወደ ናይሮቢ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሄጄ ናይሮቢን እንዴት እንደሚያስተዳድሩ ጠይቄ ነበር። ነገሩ ከበደኝ፤ ከዶክተር አድማሱ እና ከዶክተር ብርሃኑ ነጋ ጋር ኸረ ለመሆኑ ከእኛ ጋር የተመረጡት ሌሎቹ እነማን ናቸው?:: ላውቃቸው ስለፈለግሁ ተገናኝተን ልንተዋወቅ ይገባል ብዬ አሰቶችን ጉትጉትሁና አንድ ቅዳሜ ከሰአት በኋላ እንሰብሰብ ተባለ።

ያን ለት ለስብሰባው ቀደም ብዬ ልድረስ ብዬ ለዘጠኝ ሩብ ጉዳይ ስደርስ ዉጭ ምንም መኪና ባለማየቴ ደንገጥ አልሁ። ከፍሉ ውስጥ ስገባ ልንሰበሰብበት የነበረቺው ክፍል ዉስጥ ሃምሳ ያህል ሰዎች አሉ:: የተመረጥነው 135 ነን:: ከእኔ ወረዳ እንኳ የተመረጥነው 6 ስንሆን የተገኘነው ሁለት ብቻ ነበርን:: ሰምን ብዬ

ስጠይቅ የማስታውቂያ ዘዴአችን ደካማ መሆኑን ተገነዘብኩ:: የመጡትን ሰዎች አኳኋን ስመለከት፣ እነኚህ አዲስ አበባን ሊያስተዳድሩ ይችላሉን? አልኩ። ረዘም ያለ ጊዜ ወስደን መሰልጠን እንዳለብን አሳሰብሁ።

ይህን የስልጠና ጉዳይ ዶክተር አድማሱም አመኑበት:: እንድንገፋበት በመደገፍ ስልጠናው ሃላፊ አደረጉኝ:: ከአንድ ድርጅት ጋር በመነጋገር የአንድ ሳምንት ስልጠና አዘጋጀሁ:: ይህም እርስ በእርሳችን እንድንተዋወቅ አደረገን። በስብሰባው መጨረሻ የምክር ቤቱን ሹማምንት ለመመራረጥ በቃን። ከንቲባ፣ ምክትል ከንቲባ፣ የምክር ቤት አፈጉባኤ፣ ም/አፈጉባኤ፣ ጸሃፊ.. ወዘተ መረጥን። እኔ በምረጡኝ ጊዜ ንግግሬ ምክንያት ስአፈ ጉባኤነት ታጭቼ ነበር። 'እኔ ያለኝ የሥራ ልምድ ብቁ ቢሆንም ሽማግሌ ስለሆንሁ፣ የኔ ዋና መድብ ምክር ወደ መስጠቱ ነው አልኩ:: ያገኘሁት ድምጽ ዝቅተኛ በመሆኑ ሳልመረጥ ቀረሁ። እንኳንም አልተመረጥሁ።

ስልጠናውን በጨረስን በሳምንቱ ለህክምና ወደ ባንኮክ ሄድኩ። ባንግኮክ እያለሁ የቅንጅት ባለስልጣኖች እስር ቤት መግባታቸውን ሰማሁ። ባንግኮክ ባልሄድ እኔም የመታሰር እድል ነበረኝ። የተመረጠው ከንቲባ፣ ስአ.አ. ምክር ቤት አፈጉባኤና ጸሃፊ የተመረጡት ጭምር ከሌሎቹ ጋር እስር ቤት ገቡ።ወገቤን በጣም ስላመመኝ ነበር ወደ ባንግኮክ የሄድሁት:: ከህክምናዬ በኋላ ለማገገም ልጄ ወደ ቻይና ወሰደኝ:: እዛ እያለሁ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ እንደማይገባኝ ምክር ተሰጠኝ:: ብመለስ እኔም እስር ቤት እንደምገባ ተፈርቶ ነበር:: እኔ ይሄን ያህል የታወቅሁ ፖለቲከኛ ስላልሆንሁ፣ ኢህአዴግን የሚያስቆጣ የተናገርሁት ነገርም ስላልነበረ አያስሩኝም ብልም በተለይ ግደይ እንድመለስ አልፈለገችም::

በመሆኑም ከቻይና ወደ ባንኮክ ተመልሼ በዶክተሬ ከታየሁ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ስንመለስ ግደይ አዲስ አበባ ወረደች:: እኔ ወደ ናይሮቢ እንድሄድ ተወስኖ ስለነበር ወደዚያው ቀጠልሁ፤ ተሰደድሁ ማለት ነው። ግደይና ሌሎች ይፍሩ እንጂ እኔ አልፈራሁም ነበር:: አዲስ አበባ ኤርፖርት ሆኜ በተለይ ከእኔ ጋር ስአዲስ አበባ ከተመረጡት ሁለቱን ደውዬ አናግሬ ነበር። ያነጋገርኳቸው





ለጥቂት ቀናት ታስረው እንደፈቱዋቸው ነገሩኝ። ምንም አትሆንም ቢሉኝም ጉዞዬን ቀጥዬ ናይሮቢ አራት ቀናት ቆይቼ ሊያለፉኝ ቢፈልጉ የምለውን ጽፌ ወደ ኢትዮጵያ በድፍረት ተመለስሁ። እነኚያ አራት ቀናት በስደተኛ አእምሮ የሚንገዋልለውን እንድቀምስ ያስቻሉኝ ነበሩ።

አዲስ አበባ እንደደረስሁ ያልታሰሩት የአዲስ አበባ ምክር ቤት ተመራጮች አዲስ አበባን እንዲያስተዳድሩ በመንግሥት እየተገፉ መሆኑን አየሁ:: የመንግስትን ጥሪ ሊያስተናግድ እየሞከረ ያለው ለምክር ቤቱ ም/አፈጉባኤነት ተመርጦ የነበረው አቶ አየለ ጫሚሶ ነበር። ጉብተን እንረከብ ብሎ ገፋፋኝ፤ እኔ ግን ከንቲባ እንዲሆን የመረጥነውና ሌሎችም እስር ቤት ሆነው ልንቀበል አይገባም አልኩት:: ከዚህም በላይ አዲስ አበባን ማስተዳደር ትልቅ ሃላፊነትና ብቃት ይጠይቃል፤ 40 ያህል አባላት ሆነን መረከብ አይገባንም አንችልም አልሁት:: እርሱ ይህን እየገፋፋ እያለ የመንግስትን ምኞት የማልፈጽም መሆኔ በመንግስት ዘንድ ቅሬታን እንደሚያስከትልብኝ አወቅኹ::

ቀጥሎም ከፖለቲካ መውጣቴንም በመግለጽ ለምርጫ ቦርድ በደብዳቤ አቅርቤ የተሰጠኝን የፖለቲካ ካርድ በመመለሴ ከፖለቲካ እንደ ወጣሁ እንዲታወቅልኝ አደረግሁ። በዚህ ሁኔታ የፖለቲካ ሕይወቴ ተቋጨ::

## የጤና መታወክ የባንግኮክ ሕክምና

ኬንያ ስኖር ጀምሮ እልፎ እልፎ ወገቤን ያመኝ ነበር:: እንዲህ ሲያመኝ ወደ ዘመናዊ ወጌሻ (ካሮፕራክተር) እሄድና በመታሸት እድናለሁ:: አዲስ አበባ ከመጣሁ በኋላ ሲያመኝ ካሮፕራክተር ፈለግሁ። ዶክተር ሙላቱ ባፋ ከወዳጄ ከአቶ በየነ ሙላቱ ጋር አሜሪካ ሄደው የተማሩት በዚህ ሙያ ነበር። ራስ ምታትም ቢሆን ካሮፕራክተሮች የነርቭ መታወክ ነው ስለሚሉ እራሴን ሲያመኝ በየንን ወጌሻዬ እያልሁ እንዲያሸኝና እራስ ምታቴ እንዲተወኝ አድርገኝ እለው ነበር:: እውነትም ያሻሸኝና እራስ ምታቴ ይተወኛል።

ወደ ኢትዮጵያ ከተመለስኩ በኋላ ከበየነ ይልቅ ዶክተር ሙላቱ በሙያው እየሠራ መሆኑን ስለማወቅ ጠየኩት:: በወቅቱ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን ዋና ጸሐፊ ሆኖ ያገለግል ስለነበር ምናልባት በትርፍ ጊዜውም ቢሆን የወጌሻነቱን ሥራ ይሠራ እንድሆን ወገቤን እንዲያርቀኝ ጠየቅሁት:: ዶክተር ሙላቱም "አይ አሁን አልሠራም" ብሎ በሙያው ላይ ተሰማርታ ያለች የዶክተር ሰላምን ስም ሰጠኝ:: ወገቤን ስታመም ሁሌ ወድ እርሷ እሄድ ነበር:: ብዙ ጊዜ አከማኝ አድናኛለች። አሁን ግን ስላልቻለች ወደ ዉጭ ሄጄ እንድታከም መከረችኝ። የት ልሄድ ስል ኬንያና ደቡብ አፍሪቃ በሃሳቤ መጡልኝ። ስለጉዳዩ ከወዳጄ ከማሞ ገ/መስቀል ጋር ስነጋገር፣ ጠቅላላ የጤና ምርመራ በባንኮክ እንዳደረገ መከሮኝ አድራሻ ሰጠኝ።

የታይላንድ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበርን ምከር ጠይቄ ወደዚያው አመራሁ። ባንኮክ ክርስቲያን ሆስፒታል የሚባል መኖሩንና አጠገቡ ባንኮክ ክርስቲያን የእንግዳ ማረፊያ እንዳለም ነገሩኝ:: ለህመሜ ኮዲን እየቃምሁ ከግደይ ጋር በኢትዮጵያ አየር መንገድ አጎንብሼ ወደ ባንግኮክ ተጓዝሁ:: አይሮፕላን ማረፊያ እንደደረስን ተሽከርካሪ ወንበርr ቀረበልኝ:: የባንግኮከን አይሮፕላን ማረፊያ ውጣ ውረድ በወንበር ገፊዬ አማካኝነት በአጭር ጊዜ ተወጣነው:: ሻንጣችንን ተረከብንና ወደ ታክሲ ሄድን:: ታክሲው በቀጥታ ወደ ማረፊያ ሆቴላችን ወሰደን፤ ስማችንን አስመዘገብንና ወደ ሆስፒታሉ አመራን።

ሆስፒታሉ በር ላይ አንደ ደረስን ተሽከርካሪ ወንበር ቀረበልኝና ወደ በሽተኛ መቀበያ ሄድኩ:: ከእዚያም በአጭር ጊዜ ወስጥ ትኩሳቴን፣ የደም ግፊቴን ተለካሁና ዶክተር ለማየት ተሰለፍሁ:: ቅድሚያ ተሰጠኝና ዶክተሩ አየኝ። የህመሜን ከፍተኛነት አይቶ በማግስቱ ጠዋት ኤም አር አይ (MRI) ወደምነሳበት ቦታ እንድሄድ አደረገኝ:: የኤም አር አይ (MRI) ለመነሳት በጀርባዬ ለጥ ብዬ መተኛት ነበረብኝ፤ አልቻልኩም፤ ብዙ መርፌ ወግተው እንድጋደም አደረጉኝ፤ አሁንም ህመሙ በጣም ከባድ ቢሆንም ስ20 ደቂቃ ተሰቃይቼ ተነሳሁና ውጤቱን ይገና ወደ ዶክተሬ ተመለስሁ::





የኤም አር አዩን ሲያይ መተኛት አለብህ፤ ከአኔ የተሻለ ባለሙያም አጠራለሁ ብሎ ጠራ:: በማግስቱ ስኞ ጠዋት ባለሙያው መጥቶ ሲያይ አፕራስዮን መሆን አለብህ አለኝ። ተለፋዬ መድሃኒት ስጥተው ወይም አንድ ነገር አድርገው ያሸሉኛል የሚል ነበር:: አፕራስዮን መሆን ካለብኝ አሜሪካ ካሉ ልጆቼ ጋር እንድመከር አንዲት ወረቀት ጻፍልኝ ብዬው ጻፈልኝ:: ያቺን ወረቀት ለሩትና ለአማኑኤል በፋክስ ላክሁ:: እንደአድል ሆኖ የአማኑኤል ጓደኛ Neurosur-gen በመሆኑ የያዘኝ በሽታ ባለሙያ ነበርና አፕራስዮን ከመሆን ሌላ አማራጭ እንደሌለኝ ነገራቸው።

ለህከምና ወደ ባንግኮክ የመሄዴ ነገር ሁሉም ዘመዶቼና ልጆቼ አውቀዋል። አህቶቼ ከአሜሪካ፣ ናታን ከቤጂንግ በስልክ ተነጋገሩበት:: ናታን ከቤጂንግ ማከለኞ ጠዋት መጣ:: ረቡእ ከሰአት በኋላ ይህ ታላቅ አፕራስዮን ሲደረግ ተወለነ:: ከዛ በኋላ የሆነውን ነገር መዘገብ ጸሃፊንም አንባቢንም ያደከማልና አለፍ አለፍ እያልሁ ላውጋችሁ።

ሁለንተናዬን ለእግዚአብሐር ደግሜ ስጥቼ ወደ አፕራስዮን ከፍል ገባሁ:: ግደይና ናታን ወደ አንዲት ማረፊያ ቦታ ሊተከዙና ሊቆዝሙ ሄዱ:: አፕራሰዮኑ አራት ሰዓት የፈጀ ነበር:: ከአፕራሰዮን ወጥቼ ማገገሚያ ከፍል ሆኜ የግደይን ድምጽ ሰምቼ ስለነበር፣ ባለኝ ሃይል ድምጼን ከፍ አድርጌ በእንግሊዝኛ ቋንቋ "ግደይ ከፍተኛ ህመም ላይ ነኝ፣ አባከሽ መድሃኒት እንዲሰጡኝ ንገሪያቸው ማለቴን አሁን ድረስ እየቀለዱ ያወራሉ:: እየቆዘመ የነበረው ናታንም ሳይቀር በጥያቄዬ መሳቅ ጀመረ:: ማስታመም ማለት እንደዚህ ነው?

መኝታ ከፍሌ በጀርባዬ ነበር የተኛሁት:: ከአህቶቼና ልጆቼ ውጭ ከአሜሪካ ደውሎ ያናገረኝ ወንድም ብርሃኑ ደረሰ ነበር:: "ይሄውልህ ተንጋልዬልሃለሁ" ስለው፡ "ምናልባት ይበልጥ ወደ እርሱ እንድታይ ጌታ ፈልጎ ይሆናል" አለኝ:: በእውነቱም የጌታን ፊት አሻ ነበር::

የኢዮብን መጽሐፍ በማለተዋል አነበብሁ። ሰው ለምን ይታመማል? የአእምሮም

ሆነ የስጋ ስቃይ ለምን ይደርስበታል? የኢዮብ ስቃይ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። ኢዮብ የደረሰበት መከራ በሠራኸው በደል ምክንያት ነው እያሉ እጽናኞቹ ይነግሩት ነበር፡፡ እኔም ይህ የደረሰብኝ ፖለቲካ ዉስጥ በመግባቴ እግዚአብሔር እየቀጣኝ እንደ ሆነ የሚነግሩኝ ጥቂት አልነበሩም፡፡ በተለይ ግደይ አጥብቃ ትለኝ ነበር፡፡ እኔም ቢሆን ጌታ ሆይ ነው እንዴ? ብየ ጠይቄያለሁ፡፡ እኔም ጌታን "ፖለቲካ ዉስጥ የገባሁት ጸልዬ ነው" ተሳስቻለሁን? ልትቀጣኝ ነው እንዴ" ካልኩት በኋላ "የምትቀጣው የምትወደውን ነውና እሺ ልቀጣ" አልኩት። በዚየን ወቅትና ከዛም ከወጣሁ በኋላ ሰው ለምን ይታመማል? ስል አሰላስልኹ።

## ሰው ለምን ይታመማል?

ሰው ሲታመም በሽታውን እግዚአብሔር እንደላከበት፡ ሰዎች ያስባሉ፡፡ የኢዮብ ሚስት እንደዛ አስባለች፡፡ ኢዮብ እራሱም ሲመልስ፡ "እግዚአብሔር መልካም ነገር ሲሰጠን በደስታ እንቀበላለን፡ ታዲያ መከራ ሲያመጣብን በእርሱ ላይ ማጉረምረም ይገባናልን?" ሲል መመለሱ የደረሰበት መከራ ከእግዚብሔር እንደሆነ የገመተ ያስመስለዋል፡፡ ሆኖም የኢዮብ ጥያቄ ለየትኛው በደሌ ነው የተቀጣሁት እያለ እንደነበር እናውቃለን። የኢዮብ ወዳጆች ደጋግመው ለኢዮብ ያሳሰቡት የስቃዩ ምክንያት የራሱ በደል መሆኑን ነበር።

"በእግዚብሔር ፊት ጻድቅ ሊሆን የሚችል ሰው አለን? ወይስ በፈጠሪው ፊት ንጹህ የሚሆን ሰው ይገኛልን?" (ኢዮብ 4፥17) የኢዮብ እጽናኝ ኤልፋዝ እንዲህ በማለቱ "ኤልፋዝ ሆይ እውነትህን ነው" እንላለን?

ክርስቶስ በቀራንዮ መስቀል ላይ ለእኔ በመሞቱ ኃጢአቴን ምስራቅ ከምእራብ እንደሚርቅ ስላራቀልኝ ንጹህ ሆኜ ፊቱ ልቀርብ እችላለሁ ልንል እንችላለን። ይህም ቢሆን ስንታመም ምላሻችን ለምን ታመምሁ ሳይሆን ማረኝ ማለት እንደሆነ ያገራችን አባባል ያስታውሰናል፡፡

ሌላው ትልቁ ጥያቄ ስለ ቅጣት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤ "ልጄ





ሆይ! የእግዚአብሔርን ተግሳጽ አታቃልል በቀጣህ ጊዜም ተስፋ አትቁረጥ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚወደውን ይገሥጻል፤ እንደ ልጅ አድርጎ የሚያየውንም ይቀጣል .. ወላጆቻችን መልካም መስሎ እንደታያቸው ለጥቂት ጊዜ ቀጥተውናል፤ እርሱ ግን የቅድስናው ተካፋዮች እንድንሆን ለጥቅማችን ይቀጣናል" (ዕብራ 12፥5፤6,10)

እግዚአብሔር ልጆቹን የሚቀጣው እንዴት ነው?፡፡ በዱሮ ዘመን እግዚአብሔር የእሥራኤልን ልጆች እንዴት እንደቀጣ እናውቃለን፡፡ እኛን ዛሬ የሚቀጣው እንዴት ነው? በህመም ይሆን? ሊሆን ይችላል። ለዚህ አስተሳሰብ ፍንጭ የሚሰጠን ጳውሎስ ስለእንድ ጭንቀቱ ያለው ነው።

"ከተገለጠልኝ ታላላቅ ነገሮች የተነሳ እንዳልታበይ ሥጋዬን እንደ እሾህ የሚወጋ ሥቃይ ተሰጠኝ፤ ይህ የሰይጣን መልእክተኛ በመሆን እየጎሸመ በማሰቃየት እንዳልታበይ ያደርገኛል። ይህ የሚያሰቃየኝ ነገር ከእኔ እንዲወገድልኝ ጌታን ሦስት ጊዜ ለመንሁት። ነገር ግን እርሱ "የእኔ ኃይል የሚገለጠው በአንተ ደካማነት ስለሆነ ጸጋዬ ይበቃሃል" አለኝ።

በዚህ ጥቅስ ሐዋርያው ጳውሎስ በአንድ ችግር ይሰቃይ እንደ ነበር ይታያል። "ሥቃይ ተሰጠኝ" ይላል፡፡ ምን እንደሆነና ማን እንደሰጠው አይናገርም፡፡ ሰይጣን መጎሸሚያ እንዳደረገው ስለሚናገር ሰይጣን እንዳልሰጠው እንገምታለን። ይህ እሾህ እንዲወገድለት እግዚአብሔርን ሶስት ጊዜ እንደጠየቀውም ይነግረናል። ለችግሩ ፈውስ ጠይቆአል ማለት ነው፤ አልተፈወሰም፡፡

እንደታመምህ ቆይ፤ አልፈውስህም፤ ሆኖም ሥቃይህን ለመቋቋም የሚያስችል <u>ጸጋ</u> እሰጥሃለሁ ተባለ። <u>ጸጋዬ ይበቃሃል</u> አለው። ይህች ለሁላችን ለኛም የምንላት ነች፤ በጀርባዬ የሠገሰጉትን ስከሩዎች (ርዝመታቸው 7 ሳ.ሜ. የሆኑ ስድስት ስከሩዎችና ያያያዙዋቸው ሌሎች ምስማሮች) እያሉ መራመድ የቻልኩት በእርሱ ጸጋ ነው ማለቴ ነው። እንዲሁም ነው። ያም ሆነ ይህ፣ የጳውሎስ ሥቃይ

የእግዚአብሔር እርጩሜ ነውን?

ሲ. ኤስ. ሉዊስ የሚባለው ታዋቂው አስተዋይ ክርስቲያን ከጻፋቸው መጽሐፍ አንዱ THE PRO8LEM OF PAIN የሚል ነው:: በዚህች መጽሀፉ ችግር፣ ህመም፣ ስቃይ፣ የሰው ዉድቀት ዉጤት ናቸው ይላል:: በአለም ከተከሰቱትና ከሚከሰቱት ሰቃዮች አራት አምስተኛው ሰው እግዚአብሔር ከሰጠው ነጻ ፈቃድ የተነሳ ሰው በራሱና እርስ በእርሱ የሚያደርገው ነው ይላል:: ስቃይ ከሰይጣን መሆኑን የሚጠቅሰው የኢዮብን ታሪክና ለ18 አመት ጎብጣ የነበረቺውን ሴት፣ ጌታ ኢየሱስ ሲፈውሳት "በሰይጣን ታስራ ስትሰቃይ ኖራለች" ያለውን ነው።

ሌላው የጠቀሰው በዮሐንስ ወንጌል ምእራፍ ዘጠኝ መጀመሪያ የተጠቀሰውን እውር ሆኖ የተወሰደውን ሰው ነው:: "መምህር ሆይ! ይህ ሰው ዕውር ሆኖ የተወሰደው በማን ኃጢአት ነው? በራሱ ኃጢአት ነውን ወይስ በወላጆቹ? ብለው ደቀ መዛሙርቱ ጠየቁት":: በደቀመዛሙርቱ አስተሳሰብ እውርነት በኃጢአት ምክንያት በሰው ላይ የሚደርስ እንከን ነው:: ኢየሱስ አሰተሳሰባቸውን አላረመም:: ቢሆንም የዚህ ሰውዬ እንከን የእርሱ ወይንም የወላጆቹ ኃጢአት ውጤት አለመሆኑን ገልጾ ፈውሰው። "ይህ የታወረው በእርሱ ወይም በወላጆቹ ኃጢአት ምክንያት አይደለም" አለ። (ዮሐ. 9፥3) የኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን አስተሳሰብ አለማረም በሰው ላይ የሚደርስ እንከን በሰውዬው ምክንያት ነው ማለት ነው ሊባል ያስችላል። በሌላ ቦታ አልጋውን ተሸከሞ እንዲሄድ ያደረገው ሽባ ሰውዬ አልጋውን በሰንበት ቀን በመሸከሙ የአይሁድ ባለስልጣናት ሰውዬን ወቀሱት:: ጌታ ኢየሱስ ሰውዬውን "እነሆ አሁን ድነሃል! ከዚህ የባሰ ነገር እንዳይደርሰብህ ከእንግዲህ ወዲህ ኃጢአት አትሥራ" አለው:: እንዲህ ሲል ሰውዬው ሽባ የሆነው በኃጢአቱ ምክንያት ነው የሚሉም አሉ።

ሲ. ኤስ. ሉዊሰ በተጨማሪ የጠቀሰው አንድ የቤተክርስቲያን አባል በኃጢአት ሲወድቅና አልታረም ሲል ቤተ ክርስቲያን እርሱን ስትቀጣው "በኃጢአት የተሞላው የዚህ ሰው ሥጋ ይፈርስ ዘንድ ለሰይጣን አሳልፋችሁ ልትሰጡት ይገባል" (1ቆሮ. 5፥5) ያሰውን ነው። በአጠቃላይ ህመም ወይም ስቃይ ከሰይጣን





ጋር ይያያዛል ማለት ነው።

ይህንን ሁሉ ከእኔ ጊዚያዊ የወገብ በሽታ ጋር ስመለከተው የታመምኩት በኃጢአቴ ምክንያት ከሆነ በየትኛው ኃጢአቴ ብዬ ጠይቄአለሁ:: ገና ናይሮቢ ሆኜ ይህን የሚመላለስብኝ የወገብ በሽታ አንድ እንግሊዛዊ ዶክተር መርምሮኝ ነበር:: መርምሮ ሲጨርስ "ችግርህን አያለሁ፤ አሁን ምንም ማድረግ አያስፈልግህም፤ ወደፊት ግን ኦፕራሲዮን መደረግ ሳያስፈልግህ አይቀርም" ብሎኝ ነበር። ሌላው ይሄው ዶክተርና ሌሎችም ለወገቤ በሽታ መንስኤ ሊሆን የሚችል የማስታውሰው ነገር መኖሩን ጠይቆኛል:: 'ከባድ ነገር ለማንሳት ሞክረሃል ወይ' ሲል::

በልጅነቴ ሚኛ እያለን ላንድ ለምትታሰብ ላም መኖ ከማሽላ እርሻ ዉስጥ ብዙ አገዳዎች ሰብስቤ በትከሻዬ ተሸክሜ ከብዛቱ የተነሣ ብዙ ጊዜ እያሳረፍሁ ቤቴ አድርሼ ነበር፤ ሌላ ሊታወሰኝ የቻለ ሸክም አልነበረም:: ስለሆነም እነዚህ ምክንያቶች እንጂ ፖለቲከኛነቴ ባንግኮክ ወስዶ ለዛ ታላቅ ኦፕራስዮን ህክምና አልዳረገኝም አስብሎኛል።

በእርግጥ ስንታመም የጌታ እርጬሜ ትሆንን ብለን መጠየቅ መልካም ነው። በማውቀውም ሆነ በማላስታውሰው ኃጢአቴ እየቀጣኸኝ ከሆነ ኃጢአቴን አሳየኝ፤ ታላቁ ምህረትህ ይጎብኘኝ ማለት ይገባናል። "እግዚአብሔርን ለሚወዱና እንደ ፈቃዱም ለተጠሩት ሰዎች እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ለጥቅማቸው እንደሚያደርግላቸው እናውቃለን"። (ሮሜ. 8፥28) የሚለውን ማስታወስ አለብን። እኔም በዚህ ጊዜ አስታውሼዋለሁ::

***

ፖለቲካ ዉስጥ በመግባቴ እንደ ተመኘሁት አልሆነልኝም:: ክርስቲያን ፖለቲካ ዉስጥ ገብቶ ሕዝብን መምራት፣ ማገልገልና በልዩ ልዩ ጊዜያት የክርስትናን መርሆ የማይቃረኑ ህጎች (ነጋሪት ጋዜጣ) ማውጣት አስፈላጊ ነው በማለት ገብቼ ነበር:: ያ ፍላጎቴ ተቀስበሰ፤ አብረውኝ የነበሩት የቅንጅት መሪዎች እስር ቤት ገቡ:: እኔም በወቅቱ አዲስ አበባ ብሆን ኖሮ ለአጭር ጊዜም ቢሆን መታሰሬ

አይቀርም ነበር። እህቴ ጽጌ እንደምትለው በዚህ ጊዜ ታምሜ ወደ ባንግኮክ በመሄዴ እግዚአብሔር ለእኔ መልካም ነገር አደረገልኝ እላለሁ።

ለአስር ቀን ያህል ሆስፒታል ከተኛሁ በኋላ ወጣሁ፤ ናታንና ቤተሰቡ በዚያው በአንዲት ግሩም የታይላንድ ባህር ጠረፍ መዝናኛ ቦታ ለአስራ አምስት ቀን ሊያዝናኑን ወሰዱን፡፡ ከዚያ ስንመለስ ሶስት ቀን ያህል ባንኮክ አደርንና ለአንድ ወር ተጨማሪ አረፍት ወደ ቤጂንግ ሄድን፡፡ እዛ ሆኜ ከከተማ ጋር በቴሌፎን ስንነጋገር ቁጭ ማለቱ ስለቸኝ ስለው "ታሪክህን ጻፍ" አለኝ፡፡ "ማን ያነበዋል" አልኩት፡፡ ኢያሱና ኢየሩ (የከተማ ልጆች) ያነቡታል ብሎ አደፋፈረኝ። እንዳለውም እስካሁን ረቂቁን ካነበቡት አነርሱ ይገኙበታል።





ምዕራፍ 13

# ኑሮ በአሜሪካና ሌሎች ተሳትፎዎች

አስራ ዘጠኝ ዓመት ናይሮቢ ከኖርን በኋላ የት እንደምንኖር ስንነጋገር አሜሪካ ልትሆን እንደምትችል አስበንበት ነበር። የደርግ ስርአት የተገረሰሰ ከመሆኑም በላይ ውጭ የመኖር ነገር፣ ለሥራ ካልሆነ በቀር አይታየኝም ነበር። በትንሹም ቢሆን በአገር ቤት በመኖር አገሪቷን መርዳት አሰብን ባይ ነኝ። በደርግ ምክንያት አገራችን የሰው ሃይል መራቆትዋ በጣም ያሳዝነኛል፡፡ በናይሮቢ በኩል ወደ ዉጭ የሄዱትን ስመለከት ቆይቼአለሁ፡፡ በሄድሁበት ቦታ ሁሉ ችሎታ ያላቸውን ኢትዮጵያውያን አይቻለሁ። በአንድ ወቅት ለሥራ ላይቤሪያ ሄጄ ነበር፤ ሞንሮቪያ የገባሁት ቅዳሜ ጠዋት ነበር፡፡ በፋኦ FAO ድርጅት ዉስጥ ለመሥራት ከናይሮቢ ወደ እዚያ የሄደ ሰው አውቅ ነበር፡፡ ቅዳሜና እሁድን ከእርሱ ጋር ለማሳለፍ ስለፈልግሁ የት እንደማገኘው ማጠያየቅ ጀመርሁ፡፡

ቅዳሜ ስለሆነ መሥሪያ ቤቶች ተዘግተዋል፡፡ የኢትዮጵያ ኢምባሲን ለምን አልጠይቅም ብዬ ወደ እዚያ ደወልሁ፡፡ ስልኩን ያነሱት አምባሳደሩ ነበሩ፡፡ እራሴን አስተዋወቅሁና ይህን ወዳጄን የት እንደማገኝ ጠየቅሁዋቸው። "እኛም እኮ ልንጠየቅ ይገባል" በማለት ቀልደው ለምሳ ጋበዙኝና ከምሳ በኋላ ሊያገናኙኝ እንደሚችሉ ነገሩኝ።

ምሳ ተጋብዤ የሞንሮቪያ ከተማ ኢትዮጵያዊ መሃንዲስ የአምባሳደሩ ጸሃፊ ባለቤት ስለነበረ መጥቶ ወደ ጓደኛዬ ወሰደኝ፡፡ ወደ እርሱ ሲወስደኝ ለካ ያ ጓደኛዬ እራሱን ከኢትዮጵያ መንግስት ያራቀ በመሆኑ ከኢምባሲው ጋር ምንም ግንኙነት እንዳልነበረው ነገረኝ።

ነገሬን ላሳጥርና ጓደኛዬ አንድ ወዳጄ ጥቂት ኢትዮጵያውያንን ሰብስቧል። ወደ እዚያ አንሂድ ብሎኝ ወሰደኝ፡፡ ግቢው እንደገባን ከቤቱ ዉስጥ የሚሰማውን የኢትዮጵያ ሙዚቃ ሰማሁ፤ አገሬ የገባሁ መሰለኝ፡፡ ቤት ዉስጥ ስገባ ከነበሩት ጋር አስተዋወቀኝ፡፡ አብዛኞቹ እዚያ አገር የሚኖሩት በየመንግስት መሥሪያ ቤቶች አማካሪነት፣ በልዩ ልዩ የተባበሩት መንግስታት መስሪያ ቤት ሠራተኝነት፤ በግል ታላላቅ ድርጅቶች ማናጀርነት በመስራት መሆኑን ተረዳሁ። ሁሉም ኢትዮጵያ በነበሩበት ጊዜ ባለስልጣን እንደ ነበሩ አየሁ፡፡ እዚያ ያሉት የደርግ አስተዳደር ባስከተለው ችግር ነበር። አዘንኩ። ይቺ አንድ ምሣሌ ነች፡፡

አሁንም ቢሆን በአሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች በዲንነትና በፕሮፌሰርነት የሚያገለግሉትን ትውልደ ኢትዮጵያውያን ምሁራንን ስመለከት አዝናለሁ፡፡ ከእነኚህ ዉስጥ አብዛኞቹ ኢ.ህአዴግ ስልጣን እንደያዘ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ያባረራቸው ናቸው። ከጥቂት አመታት በፊት ከኢትዮጵያ ለጉብኝት ወደ አሜሪካ መጥቼ በነበረበት ወቅት አንድ ሰው "እገር እንዴት ናት?" አለኝ፡፡ ጥያቄው ድርቁን በተመለከተ ስለነበር፡ "ኢትዮጵያ የተራበችው ምግብ ብቻ ሳይሆን ችሎታ ያላቸው ሠራተኞችም በማጣት ነው" አልኩት። ይህ አሁንም እውነት ነው። ተቀጥሬ ለመሥራት ባይሆንም ወደ ኢትዮጵያ ያስመለሰኝ ይሄው ነበር። ሌላው ምክንያቴ "ጋሼ መባልን ለመኰምኰም ነበር"።

አሜሪካ እንድንኖር ከሚፈልጉት ዋናዋ ልጄ ሩት ነች፡፡ ስለዚህም ለሚመለከተው የአሜሪካ መንግስት መሥሪያ ቤት አመለከተችና ኢትዮጵያ ወደአለው የአሜሪካ ኢምባሲ ሄደን ፎርም እንድንሞላ አዘዘችን፡፡ ሄደን ሞላን፤ አስፈላጊዎችን ቅድመ ዝግጅቶቹን አሟላንና ስለተፈቀደልን ከሰኔ ወር 1994 ዓ.ም የአሜሪካ ነዋሪ ሆንን።

ሩትና ሰኪ እንደተጋቡ ይኖሩ የነበረው አፓርትመንት ተከራይተው ነበር። በተጋቡ በሁለት አመታቸው አንዲት ቅልብጭ ያለች ቤት አስገንብተው በዚያች ቤት ዉስጥ ለዘመናት ኖረዋል፡፡ በዚያች ቤት ዉስጥ ሆነው ወላጆቻቸውን፣ የሰኪን እናት ወሮ ሃናን እና እኛንም አስተናግደዋል፡፡ በዚያችው ቤት ሆነው





የወይዘሮ ሃናን ሞት መርዶ ሰምተዋል፡፡ በኋላም የለኪ አባት ሙሴ ስኪቮፊላኪስን ለአራት አመት አስተናገደውና አስታመው ሲሻላቸው ሸኝተው ነበር፡፡ ነገር ግን ወደ ኢትዮጵያ በተመለሱ በሁለተኛው አመት ሰለ ሞቱ ሃዘን የተቀመጡትም እዚያው ነበር፡፡ በዚቺው ቤት ሶስቱን ልጆቻቸውን ወልደዋል፤ ወደ ኢትዮጵያ ለየብቻቸውና ሩት ከልጆችዋ ጋር መጥተው ጎብኝተውናል።

መባ የአምስት አመት ሲሆነው ከእህቶቹ ጋር ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ጎብኝተውን ነበር፡፡ በወቅቱ ከሌሎች ዘመዶችም ጋር ለመተዋወቅ በቅተዋል። እዚህ በነበሩበት ጊዜ በአምልኮ ጊዜአችን ወላጆቻቸው ሰፊ ቤት እንዲኖራቸው ይጸልዩ ነበር። ያቺን ቤት ሸጠው ሌላ ቤት ለመግዛት ስለፈለጉ ቤቷ እንድትሸጥና ሌላ ቤት እንዲያገኙ ነበር ጸሎታቸው።

ከተመለሱ ከአንድ አመት በኋላ የጸለዩበት አዲስ ቤት አሰርተው ሰፋ ያለ ፎቅ ቤት ገቡ፡፡ እያንዳንዳቸው የየራሳቸው ክፍል አገኙ። የእኛም ወደ አሜሪካ መፍለስ እንደተረጋገጠ በአጠገባቸው ለእኛም ቤት አስገነቡልን፡፡ ጥቂት ገንዘብ ከፍለን በአሜሪካ በናታን ዋስትና ባለ ቤት ሆንን። የቤት እቃዎቹን፣ የቤት እልባሳት ሳይቀሩ ልጆቻችን አሟልተው የሞቀ ቤት ውስጥ አስገቡን። በእርጅና ጎጆ መውጣት ማለት እንዲህ ነበር፡፡ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን።

## የካንሰር ህክምና

ሃምሳኛውን የጋብቻ በአላችንን እ.ኤ.አ ግንቦት 3 ቀን 2009 አሜሪካ አከበርን። ለበአሉ ሁሉም ልጆቻችን ወደ እስተን መጥተው ስለነበር የመጨረሻው ልጃችን ጴጥሮስ ሲተሻሽኝ ደረቴ/ጡቴ ጠጠር ያለ ነገር አስተዋለ፡፡ "ምንድነው ብሎ ጠየቀኝ" ሁለቱን ጡቶቼን ሳወዳድር እውነትም የግራ ጡቴ ጠጠር ያለ ሆኖ አገኘሁት፡፡ በአሜሪካ የህክምና ዋጋ የማይቻል በመሆኑ ወደ ኢትዮጵያ ለመለስ የሚሉትን አያለሁ ብልም ወ/ሮ ሩት የዶክተር ቀጠሮ አስይዛ አስመረመረችኝ። ካንሰር እለበህ ተብዬ ጡቴን ቆርጠው ጣሉት፡፡ ኪሞ ቴራፒ ተሰጠኝ።

ቀጥሎም በጨረር ተጠበስሁ:: በዚህ ውስጥ ትልቁ ነገር የህክምና እርዳታ ስማድረግ ድጋፍ ማግኘቴ ነው። ይህም የሆነው Medical Assistance Program ውስጥ ሩት ስላስገባችኝ ነበር:: ይህ ባይኖር የማይቻል ነበር። ካንሰሩን ለማከም፣ ኦፕራሲዮን መደረጉ፣ ኪሞ ቴራፒው ምን ሊደረግ ይችል እንደ ነበረ አላውቅም:: ከኪሞቴራፒ በኋላ የምወጋት አንዷት መርፌ ዋጋዋ ከ$1000.00 በላይ መሆኑን አይቻለሁ። ጨረር ከተሰጠኝ በኋላ የተሰጠኝ የሂሳብ መግለጫ ላይ ያየሁት ጠቅላላ ድምር ከ$35.000.00 በላይ ሲሆን የኔ ድርሻ $60.00 ብቻ ነበር። ስለዚህ ሁሉ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ:: በአሜሪካ አንድኖር ያደረገኝ አንዱ ምክንያት ለዚሁ ነው እያልኩኝ ነው።

ኦፕራሲዮን ልሆን ስል አስተን ያሉትን የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ጸልዩልኝ ብዬአቸው፣ ዘይት ቀብተው ጸለየውልኛል:: ወደ ኦፕራሲዮን ከፍል መግባት አደጋ ያለው ቢሆንም ይህን በሽታ አምላኬ ለበጎ ያደርገዋል። በዚህ አድርጎ ሊወስደኝ ከፈለገም እኔም እንደ ጳውሎስ 'ብኖርም ለጌታዬ ነው፡ ብሞትም የምሄደው ወደ ጌታዬ ነው' ብዬ ህክምናዬን ቀጠልኩ:: ይህን ስጽፍ ኦፕራሲዮኑ ከተከናወነ አራት አመት ሆኖትል:: በየስድስት ወሩ ስመረመር ቆይቼ 'ምንም የካንሰር በሽታ ነገር አይታየንም' ብለውኛል። ለለዚህ ሁሉ ጌታ ይመስገን።

## ኑሮ በቴክሳስ

የምንኖረው ፍሉገርቪል በምትባል አስተን አጠገብ ያለች ከተማ ውስጥ ሲሆን የምናመልከውም ጳውሉስ ጉልላት መጋቢ ሆኖ በሚያገለግልበት በኦስተን ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ነው። ባለቤቱ የአደራ ልጃችን ቅድስት ሃብታሙ ነች። ጳውሎስና አራት ልጆቻቸው ለተወሰኑ አመታት ናይሮቢ ኖረው ወደ አሜሪካ ሲፈልሱ ወደ እዚህ ኑሩ ብላ ወደ አስተን ሩት አመጣቻቸው። ጳውሎስ የባይብል አካዳሚ ምሩቅና በመሰረተ ክርስቶስ የተቀጠረ የመጀመሪያው ወንጌላዊ ነበር።





መሠረተ ክርስቶስ ከሜኖናይት ሚሲዮን አገልግሎቶችዋን (ት/ቤቶችና ህክምና) ተረከባ ማስተዳደር ትኩረትዋ ይኸው ነበር:: የሚቀጠሩት ሁሉ የሚሠሩት በእነዚሁ አገልግሎቶች ዉስጥ ነበር:: ወንጌላዊ ብለን የምንሰይመው አልነበረንም:: ጳውሎስ የመጀመሪያው ነበር። አንዳጋጣሚ ሆኖ በዚያን ጊዜ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሊቀመንበር ስለነበርሁ ያስቀጠርሁት እኔ ነበርሁ። የተላከውም ወደ ደደር ነበር። (በዚህ ጉዳይ ስልጣንህን ተጠክምክ በማለት የከሰሰኝ የለም) ከጳውሎስ ጋር የተያያዝነው ያን ጊዜ ነበር:: ወደ ናይሮቢም መጥቶ በራዲዮ ፕሮግራም እንዲያገለግል ጠቁሜ ነበር:: ቅድስት እንደልጃችን፣ እርሱም በተጨማሪ እንደ መጋቢያችን ሆኖ በኦስተን እንኖራለን:: በአሁኑ ሰዓት ከሩት ጋር ጠያቂዎቻችንና ተንከባካቢያችን ሆነዋል። ከብዙ ጊዜ ጀምሮ የምናውቃቸው አቶ በቀለ ካሳዬና ወይዘሮ አለቱር አያናም የአስተን ነዋሪዎች በመሆናቸው የቅርብ ጠያቂዎቻችን ናቸው።

በየስድስት ወር በያመቱ ወደ አገር ቤት እንመለሳለን። ከዚህ ሁሉ ዜግነት ለምን አትሞሉም ተብለናል:: እኛም የት ብንኖር ይሻለናል ብለን አሰበናል። መኖሪያችንን ለናሰብ አንዱ መለኪያችን የዘመድ ጉዳይ ነው:: በአሜሪካም ብዙ የቅርብ ዘመዶች አሉኝ:: ሶስት እህቶቼ አሉ፣ ልጆቼም እዚሁ አሜሪካ ናቸው። በኢትዮጵያ ሶስት ወንድሞች አሉኝ:: ሌሎች ዘመዶች (በአሜሪካም በኢትዮጵያም) አሉኝ። መለኪያው ወንድም/እህት ከሆነ አሜሪካና ኢትዮጵያ ያሉት እኩል በእኩል ናቸው። የልጆቻችን እዚህ አሜሪካ መሆን ስበቱን ቢጨምረውም የኢትዮጵያ ነገር አያስችለንም:: ከባህር ዛፍ ጭሱ መአዛ ጀምሮ በእአ መንገድ ላይ የማያቸው እህዮች ሁሉ ነገር ይናፍቀናል:: ዜግነት መጠየቅ የሚለው ነገር ብዙም እንዳይጥመን አድርጎናል:: በዚህ ሁሉ እግዚአብሔር እያደረግልን ያለውን ስናይ እንገረማለን። እህቶቼ ጽጌ፣ ቤቴልና ማርታ በየጊዜው እየመጡ ይጎበኙናል፤ እኛም እየሄድን እንጎበኛቸዋለን:: አመት በአላትን አብረን እናሳልፋለን:: በየጊዜው ስልክ እንደዋወላለን:: ካገር ቤት ምን ሰማሽ ምን ሰማህ እንባባላለን:: በዚህ ነገር እንደኛ ጽጌ ነች:: ምንም እንኳ በልዩ ልዩ

ከተማ በንኖር አብረን የምንኖር ያህል ይሰማኛል። እኔ ይህን ሁሉ የእግዚአብሔር በረከት እለዋለሁ። ሌሎች ዘመዶችም አሉን፡፡ ዮናታን አሸብር እዚሁ አለ፤ በቅርብ አቢጌል አሸብር ከባለቤቷ ሱራፌልና ከህጻኑ ልጃቸው ስመረ ጋር እዚህ ለመኖር መጥተዋል።

የግደይ ወንድም ኩሉብርሃን ከባለቤቱ ከአብረኸትና ከልጆቻቸው ጋር እዚሁ አሜሪካና ካናዳ ናቸው፡፡ እህቷ ሒሪቲና ባለቤቷ ተስፋዬ ከመላ ልጆቻቸውና ልጅ ልጆቻአው ጋር ካናዳ ስለሆኑ ቅርባችን እንዳሉ እንቆጥራለን። የግደይ እህት የንግሥቲ ልጆች ጸጋ፤-ኤልሳቤጥ፣ እስቴርና ቢኒያምም ካሊፎርኒያ ናቸው። የምወዳት አክስቴ የደብሬ ልጅ አባይነሽም ከሌሎች የአክስቴ ልጅ ልጆች ከሙሉጌታ ለገስ ቤተሰብ ጋር ጽጌ አጠገብ አክላሆማ ይኖራሉ። እነኚህ ሁሉ በረከቶቼ ናቸው።

## የደስታዬ ቀኖች

ባንድ ወቅት ያለፈውን ሕይወቴን ወደ ኋላ ተምለከትሁ፤ በተለይ የተመኘኋቸውን ነገሮች ከልጅነቴ ጀምሮ እስከዚያች ቀን ድረስ አንድ በአንድ ዘረዘርሁ። በትልልቆቼ ዘንድ ያሉትንና እኔ የሌሉኝ ነገሮች እንዲኖሩኝ የተመኘኋቸውን፥ እንዲሁም ሌሎች አርዓያዎቼ የሆኑትን እንድሆን እሆን ዘንድ የተመኘኋቸውን ምኞቶች በዐይነ ህሊናዬ ቃኘሁ። የተመኘኋቸውን ሁሉ ማግኘት ብቻ ሳይሆን አንዳንዶቹን ከዚያ በላይ እንዳገኘሁ ተረዳሁ። ለዚህ ሁሉ ቸርነቱ አምላኬን አመሰገንሁ።

ትምህርት፣ ጥሩ ሥራ፥ መኪና፣ የግል ቤት፥ ትዳር። ምን ቀረኝ? አልሁ። የቀረኝ የልጆቼ ትዳር መያዝ ነበር፤ የሠርጋቸውን ቀን ስመኝ በተለይ ሩት ጉልበቴን ስማ ስትሄድ በዐይነ ህሊናዬ እየሁ፤ እንባ አነቀኝ፡፡ ያ ምኞቴ ሚያዝያ 17 ቀን 1984 ዓ.ም. ተፈጸመ። ሩትን ለለኪ (ኒኮላኦስ) ስኪቮፌላከለ ዳርን፤ የለኪ አባት በወጣትነታቸው ወደ ኢትዮጵያ የመጡ የግሪክ ተወላጅ ናቸው፤ እናቱ ወ/ሮ ሃና





ይባላሉ።

እንግዲህ እግዚአብሔርን የማመሰግንበት ብዙ የሠርግ ደስታ ቀኖች አሉኝ። የወዳጆቼን ሳልጨምር በሠርጋቸው የተገኘሁ (በሥርአቱም የተካፈልሁ) የእህቴ የጽጌ፥ የወንድሞቼ የከተማና ምስራቅ ከበደ፥ የአከሊልና የሊያ ተሾም፥ የእህቴ የአሰገደች ልጆች የግርማ፥ የጀማነሽ፤ የወንድሜ የአሸብር ልጆች፦ የሃና፥ የራሄል፥ የአቢጌል እና የዮናታን ሠርጎች ናቸው።

ሩትና ለኪን ያጋባ ወዳጃችን ዶር መለስ ወኑ ሲሆን፣ ከዚህ በታች እንደምገለጸው ናታንና ክርስቲን እኔና የክርስቲ አባት ጄሪ ስፔን፥ ጌድዮንና ሶስናን ቃል ኪዳን ያስገባን እኔና የሶስና አባት ጀነራል መኮንን ገ/ማርያም ነን፤ ማጋባት ማለት እንዲህ ይመስለኛል። ዮናታንና አደይ ሙሉጌታን ያጋባሁ እኔ ነኝ። ጽጌን ለድልነላሁ አጥላባቸው፥ ሩትን ለለኪ ስኪቮፌላከለ፥ ሃናን ለጉልላት ታደሰ፥ አቢጌልን ለሱራፌል ወስንየለህ እጃቸውን ይዤ ያስረከብሁ እኔ ነኝ። በግርማና አይናለም ተሾመ ሠርግ ላይ የሠርግ መልእክት አቅርቤአለሁ፤ በሌሎቹ ላይ ተመልካች ነበርሁ።


ጽጌን ለድልነላው አጥላባቸው ለስጥ ስንሄድ


ሩትን ለለኪ ስኪቮፌላኪስ ለስጥ ይገፍ ስንሄድ



ሩት ስታገባ ከቤተሰብ ጋር



ጀማነሽ ሲታገባ ከእናቷ፣ ከትዮጵያና አክስቷ ጋር



ራሄ ስታገባ ከእናትዋ እና ከእኔ ጋር



ሃና አሸብርን [illegible]





የናታን አሸብርና ዶ/ር አደይ መሐሪትን ሲጋባ





## የጌድዮንና ሶስና፥ የናታንና የክርስቲ ጋብቻ

የእነኚህ ጥንዶች ጋብቻ ልዩ ነበር፤ ልዩ ያደረገውም የናታን የፈጠራ ሃሳብ ነው። እርሱም እኛ አባቶች ተጋቢዎቹን ቃል ኪዳን ማስገባታችን (ማጋባታችን) ነው። የክርስቲ አባት ጄሪ ስፔይንና እኔ ናታንና ክርስቲን፥ የሶስና አባት ጀነራል መኮንን ገብረ ማርያምና እኔ ጌድዮንና ሶስናን ቃል ኪዳን ማስገባታችን (በእውነቱ ማጋባታችን) ነው።

(ሀ) ሰኔ 8 ቀን 1988 ዓ.ም. (June 15/1996) ስፕሪንግፊልድ መዘሪ ናታንና ክርስቲን ተዳሩ፤ ሠርጉ በዚህች አነስተኛ የአሜሪካ ካተማ የሆነው የክርስቲ ወላጆች እዚህ ስለሚኖሩ ነው። በዚች ከተማ ኢትዮጵያውያን ስለሌሉ የሃበሻ ቤተክርስቲያን የለም፤ ዘመዶች ተሰባስበን ወደ እዚህ መጥተን በፈረንጆች ደንብ እርብ ማታ የማታ ግብዣ፣ በእነርሱ አባባል ሪኸርሳል ዲነር (REHEARSAL DINNER) አደረግን። የሃበሻውን ምግብ ሁሉ ግደይና ሩት እስተን አዘጋጅተው ይዘው መጡ።

እራት ከተበላ በኋላ የጋብቻው ሥርአት ሂደት ተሞከረ። በማግስቱ ቅዳሜ ከሰአት በኋላ ጋብቻው ተፈጸመ። ማታ በከተማዋ በምትገኝ ትልቁ ሆቴል የክርስቲ ወላጆች መደበኛው የእራት ግብዣ ተደረገ። ሙሽሮቹ ጫማም ላይሰሙ ለጨረቃ ማራቸው ሳናውቀው ተልይተውን ሄዱ። እኛም በማግስቱ ወደ የመጣንበት ተመለስን። ራቅ ካለ ቦታ ከካሊፎርኒያ የመጡት ዶ/ር ተስፋጽዮን ደሰለው፣ አቶ ተከሌ ገብረ ሥላሴ፣ ወ/ሮ በላይነሽና ዶ/ር አረጋ፥ ወ/ሮ ጸጋ መንግስቱ ከካሊፎርኒያ፤ ጽጌ ከኦክላሆማ ሲቲ፤ ቤቴልና ማርታ ከዳላስ፤ ስኪ፥ ሩት፥ ሊይና ናኦሚ እኛን ይዘው ወደእስተን ተመለስን።

ክርስቲንና ናታን ከዛ በኋላ ያየናቸው ወደ ዋሺንግተን ዲ.ሲ. ሄደው የተከራዩትን ቤታቸውን ሲያዘጋጁ ነበር፤ ሳይቆዩ ቤትም ገዝተው በገዙት ቤት ሆነው ማትያስናን ማርከስ በመውለድ የልጅ ልጆቻችንን ወደ አምስት ከፍ አደረጉልን።

(ለ) ሐምሌ 12 ቀን 2000 ዓ.ም (July 19, 2008) ጌድዮን ሶስናን በምትባል

ስሜን ፔንስልቫኒያ ከላንካስተር 50 ማይልስ ርቃ በምትገኝ ትንሽ ከተማ ሰርጎ ለሶስና መኮንን ዳርነው። የሶስና ወላጆች ጀነራል መኮንን ገብረ ማርያም እና ወ/ሮ ጽሳት ሙሴ የሚኖሩት ፊለደልፊያ አጠገብ ነበር። የሚያመልኩት በዚቹው ከተማ መጋቢ እንዳልካቸው ሳህሌ በሚያገለግለው ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ነው። የጋብቻውን ፕሮግራም የመራው ወንድም እንዳልካቸው ሲሆን፣ የጋብቻውን መልእክት ያቀረበው ወዳጃችን ፓል ጊንግሪክ ነበር:: የጋብቻውን ስነስርአት ያካሄድነው ሁለቱ አባቶች ነበርን። ከቃል ኪዳኑ በኋላ በዛው በተዘረጋው ትልቅ ድንኳን ውስጥ የእራት ግብዣ ተደረገ። በአሜሪካና በካናዳም ያሉ ዘመዶችና ወዳጆችም ለመገናኘት ምክንያት ሆነን። ሚያዝያ 9 ቀን 2002 (April 17, 2010) ሜሮንን በመውሰድ ስድስተኛ የልጅ ልጃችንን አስገኙልን።


ጀንራል መኮንንና እኔ ሶስናንና ጌዴዎንን ስናጋባ
ማጋባት እንዲህ እንደሆነ ያስተውሏል


ጄሪ ስፒይንና እኔ ናታንና ክርስቲን ስናጋባ





## መደምደሚያ

ማስሎ የሚባል ሰው የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቶችን አስመልክቶ በቀመረው ንድፈ ሃሳብ (ቲዮሪ) መሠረት የማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር ፍላጎቶች በአምስት ደረጃ ይመደባሉ።

የመጀመሪያው:- ምግብ፥ ውኃ፥ መጠለያ፥ እንቅልፍ ወዘተ ናቸው።

ሁለተኛው:- ከማንኛውም ዓይነት አደጋ መጠበቅ፥ ከፍርሃት ነጻ መሆን፥ ወዘተ ናቸው::

ሦስተኛው:- የሰው ፍላጎት የመወደድና የመውደድ፥ ወደዳጅነት፥ ፍቅር ወዘተ ናቸው::

አራተኛው:- የመከበር ፍላጎት፥ ተቀባይነት የማግኘት ፍላጎት፥ በሰውም በራስም የመተማመን ፍላጎት፥ ኩሩነት ወዘተ ይገኙበታል::

አምስተኛውና የመጨረሻው ደረጃ:- ሊኮን የሚቻለውን መሆን፥ በነገር ሁሉ መካናውን፥ የመሠረታዊ ፍላጎቶች መሟላት፥ የይበቃኛል ስሜት ወዘተ ናቸው።

ከተባበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ማሕበሮች (ዩ. ቢ. ኤስ) ጡረታ ወጥቼ፥ በአዲስ አበባ ቤት ገዝቼ፥ በቤት ዉስጥ የሚያስፈልጉ ደረጃቸውን የጠበቁ እቃዎች ናይሮቢ ገዝቼ፣ በአይሮፕላን አስመጥቼ፣ መኪና ገዝቼ የተደላደለ ኑሮ እየኖርኩ አገኘሁ። በዚህ ዓለም መለኪያ የሚያስፈልገኝ ሁሉ አለኝ።

ከዚህ ሁሉ በላይ ከአምላኬ ጋር ሰላም አለኝ። በአዲስ አበባ ኑሮ እንደ ጀመርኩ የአብያተ ክርስቲያን ሕብረት በደብረ ዘይት ሰሚናር አዘጋጅቶ ስለነበር በዚያ ሰሚናር ላይ ለመካፈል መኪናዬን እየነዳሁ ሄድሁ። በአንዱ ክፍለ ጊዜ የወርልድ ቪዥን ባልደረባ የነበረው ዶ/ር ጥበበ አሼቴ የማስሎን ቲዎሪ መሠረት በማድረግ ስለ ሰው ፍላጎቶች ገለጻ ሲያደርግ የራሴን ፍላጎቶች መሟላት አለመሟላት ገምግሜ ነበር። በሁሉም ደረጃዎች እንዳለፍሁ አየሁ። በተለይ በዚያን ወቅት የቀረኝ ነገር እንደሌለ ተረዳሁ።

በሥራ ዓለም (በነበርኩበት መሥሪያ ቤት) ከደረሰሁበት ደረጃ በላይ የተመኘሁትና የቀረብኝ የለም፤ በደረስሁበት ደረጃ ተከብሬ፥ ማድረግ የሚገባኝን ነገሮች ሳልቸገር እያከናወንሁ ነበር፤ በአለቆቼና ሥራ ጓደኞቼ ተከብሬና ተወድጄ ነበር ጡረታ ልውጣ ብዬ ነው የወጣሁት።

አሁን ልሠራ የሚገባኝ ያልሠራሁት ቀረኝ የምለው ሳይኖር ወደ አልጋዬ አሄዳለሁ፤ ምሳዬን በልቼ ወደ መሥሪያ ቤት ለመሄድ አልቸኩልም፤ ያልሠራሁት የቤት ሥራ ይኖር ይሆን ብዬ አልጨናነቅም፡፡ መልካም የጡረታ ኑሮ ማለት ይህ ነው!

አሁን የምገኝበት ሕይወት «በበቃኝ ስሜት» ውስጥ ነው፤ በመዝሙር 23 ቁጥር አንድ "እግዚአብሔር እረኛዬ ስለሆነ የሚያስፈልገኝን ሁሉ አላጣም" እንዳለው "የሚያስፈልገኝን ሁሉ ሰጠኝ" ለማለት እደፍራለሁ፡፡

በዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ምዕራፎች ላይ እንደ ገለጽኩት የከብቶች እረኛ ነበርሁ፤ ከብቶቼ ሳር የሚገኝበትን መስክ አያውቁም ነበር፤ ሊያውቁም አይችሉም፡፡ ጥሩ ግጦሽ ያለበትን የማውቀው እኔ እረኛቸው ስለ ነበርኩ ወደ እዛ እመራቸው ነበር። ልጁ እንዲሞትልኝ የሰጠኝ እረኛዬ የሆነው እግዚአብሔር በለመለመ መስክ አውሎ አሳደረኝ፡፡ በቃኝ፣ ጠግቤአለሁ ወደምልበት ደረጃ እንድደርስ አደረገኝ፡፡

***

ይህ ረቂቅ ሲጠናቀቅ ለገጣፎ በመኖር 86ኛ ዓመቴን ጀምሬአለሁ፡፡ የዳዴ ቀናቶቼ ሳይጨምሩ ይህን ያህል ዓመታት ለጌታ ሥራ ሮጫለሁ፡፡ ሩጫዬን ወደ መጨረሱ የተቃረብኩም ይመስለኛል፡፡ አንድ ነገር አውቃለሁ የዘውድ አክሊል በዓሌ ቀን ተቃርቧል። በወጣትነቴ ዘመን ህይወቴን የሰጠሁት፣ ሩጫዬን





ያስጀመረኝ፣ የሰጠሁትን አደራ እንደሚጠብቅና ሩጫዬን እንደሚያስጨርሰኝ አውቃለሁ። (2 ጢሞ 1፥12) ስለዚህ እኔም እንደ ጳውሎስ (2 ጢሞ. 4፥6-8) እንዲህ እላለሁ። «የሰጠሁትንም አደራ እስከዚያ ቀን ድረስ ሊጠብቅ እንዲችል ተረድቼአለሁ።»

ሃሌሉያ

ሃሌሉያ

# ቅድመ ኅትመት የአንባቢዎች አስተያየት

## የአብሮአደግ አስተያየት

ትውስታዬ ብሎ የሰየማት የአብሮ አደጌና ውድ ጓደኛዬ ሚሊዮን በለጠ በአጭሩ የነደፈው የሕይወት ታሪኩ ትኩረት መጽሐፍ ቅዱስና መልእክቱ ነው። በመሆኑም ዷብዛኛው የሥራ ዘመኑ መጀመሪያ ለሃገሩ በኋላም ለመላው አፍሪቃ ሕዝብ የመጽሕፍ ቅዱስ ጉዳይ ሆነ።"እምነት ከመስማት ነው፤ መስማትም ከእግዚአብሒር ቃል ነው፤ (ሮሜ 10፥17) ሰው ቃሉን አንብቦ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አንድ ግል አዳኙ በመቀበል የአግዚአብሔር ልጅ እንዲሆን፡ ከዘላለም ኩነኔ ወደ ዘላለም ሕይወት እንዲገባ ነው። ይህ ነው የሚሊዮን ዓላማ።

ይህ የእርሱ ዓላም ሲሆን የእግዚአብሔር ጥበቃና ምሪት እንዳልተለየው ትውስታዬ ብሎ የሰየማት ድርሰቱ ትተርካለች።

በሐረርጌ ክፍለ ከተማ በወበራ አውርጃ በደደር ተወልደን እስከ ስምንተኛ እዛው ተምረን፥ በዚያን ጊዜ ዘመዶቻችን እንደመሰላቸው ወደሸዋ ተሰደን፥ በአዲስ አበባ ተግባረ ዕድ ት/ቤት ስለ ራዲዮ ተማርን። አርሱ በአሜሪካ እኔ በአዲስ አበባ የኮሌጅ ትምህርት ለመከታተልና ከኮሌጅ ለመመረቅ በቃን፤ የአብሮ ጉዞአችን ጉዞ ለብቻው መጽሐፍ ይወጣዋል። ክብር ለአምላካችን ይሁን። ይህቺን ትውስታዬን ላነብ ያስታወሰኩትና ያስገረመኝ በ11 አመት ይለያይ አንጂ የጋብቻችን ቀን አንድ መሆኑ ነው፤ ሚያዝያ 25 ቀን 1951 እና 1962 ዓ.ም. እርሱ እህት ግደይን እኔ ኤልሳቤጥን ስናገባ እርሱ ለእኔ፥ እኔም ለእርሱ ሚዜ ነበርን።

በእነኚህ ዘመናት በሩቅም ሆነን በሩቅ የሚሊዮንን ሕይወት ስመለከት ለጌታ ያለውን ፍቅርና በቤተ ክርስቲያናችን ጅማሬ ስለነበረው ተሳትፎ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። እንዲሁም ስለአድገቱ ሁሉ፥ ከአስተማሪነት ወደ ዲሬክተርነት፤ ከስንበት ት/ቤት አስተማሪነትወደ እጥቢያ መጋቢነትና የቤተ ክርስቲያን መሪነት፤ ቤተክርስቲያንን በአህጉር (በአፍሪቃ) ከመወከል፥ አህጉርን በአለም ሚኖናይቶች ህብረትመወከል በኋላም ፕሬዚደንት መሆኑ፤





የኢትዮጵያን መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር አቁቁሞና መርቶ የአፍሪቃ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበሮች ዋና ጸሃፊ መሆኑ። ይህ ሁሉ ያስታዩና አግዚአብሔር ይመስገን ያሰኘኝ ነው።

ወደ አገር ቤት ስንመለስ የልዩ ልዩ ድርጅቶች ተባባሪ መሥራች መሆኑ፥ የተስፋ ድርጀት፥ የአፍሪቃ ኢንተርፕራዝ፥ ራዕይ አሳታሚ ድርጅት። በተለይ ራዕይ የእርሱ ራእይ ስለሆነ እኛ አባላቱ አምላክ ይበለጥ ይባርከው አያልን ነው።

ሚሊዮን መጽሐፍ ማንበብ ይወዳል፤ ሌሎችም እንዲያነቡ ይፈልጋል።" አንብብ፥ አንበቢ፥ አንብቡ" የሚል ታፔላ/ምልክት እየለጠፈ በአዲስ አበባ ራዕይ መጽሐፍ መደብሮችን፥ መቀሌ በነበረበት ጊዜ ብርሃን መጽሐፍ መደብርን የከፈተው ስለዚህ ነው። ቻፕሎችን ከመክፈት ሌላ እነኚህ ሁሉ ዋጋ ያስከፈሉት ስለሆነ፥ ሚሊዮን የሰጠው ጊዜውን ብቻ ሳይሆን ገንዘቡንም ነው። <u>በራዕይ አሳታሚ፡ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር</u> ትልቅ የከሰዮን ድርሻ ያለው እርሱ ነው።

በአጭሩ የሚሊዮን "ትውስታዬ" ጓደኛችን እንግዳ አሰፋው (እሁን ዶር.) እንዳለው

Only one life, it will soon be past. What is done for Christ will last>

አንድ ሕይወት ብቻ አለ. አርሱም ያልፋል፤ ለክርስቶስ የተሠራ ይዘልቃል።

ትዉስታዬን አንብቧት፥ ትባረካላችሁ።

ፀጋ ወልደማርያም (ኢንጅነር)

ከአቶ ሚሊዮን ጋር ከተዋወቅን ከሃምሳ ዓመት በላይ አስቆጥረናል:: ትውውቃችን የጀመረው በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር አንዳገለግል ከጋበዙኝ በኋላ ነበር:: ከዚያን ጊዜ አንስቶ በአገር ውስጥና በውጭ አገር አብረን እያገለገልን ወዳጅነታችንም እየተጠናከረ፣ ግማሽ ክፍለ ዘመን አብረን ዘለቅን::

«ትውስታዬ» በሚል ርዕስ ያዘጋጀነውን የመጽሐፍ ረቂቅ ሳነብ፣ የመጽሐፍ ገጾችን ማገላበጥ ሳይሆን ራሱን ሚሊዮንን የማንበብ ያህል ‹ቅርብ› ሆነልኝ፤ እርሱ ወደ ወረቀት ለወጣቸው እንጂ ትውስታዎቹ ለእኔም ትዝታዎቼ ናቸው::

በትውስታው ያካፈለን ከልጅነት አስከ ጉርምስናውና ድረስ ያለፈባቸውን የሕይወት እርከኖች አጅግ መስጠውኛል:: ከአረኝነት አስከ ዓለም አቀፍዊ ድርጅት ዲሬክተርነት መድረስ ለመቻል ጠንካራ ስብዕናን ይጠይቃል፤ ሚሊዮን ያን ያህል ጠንካራ ሰው መሆኑን እመሰክራለሁ::

ሚሊዮን ከአረኝነትና ከቄስ (አብነት) ትምህርት ቤት ተነስቶ የአስኮላና የኮሌጅ ተማሪ፣ መምህር፣ የአስተዳደር ኃላፊ፣ ዲሬክተር፣ የመሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሽማግሌ፣ መጋቢ፣ ሊቀ መንበር፣ በሜኖናይት ዓለም አቀፍ ኮንፌረንስ ተወካይ ... ወዘተ ሆኖ አሳልፏል:: በስተርጅናውም በንግዱና በፖለቲካው ዘርፍ ተሳትፏል::

ሚሊዮን በፊቱ የመጡለትን ማናቸውንም ነገሮች በቀላሉ የሚቀበል ሰው አይደለም፤ ይጠይቃል፤ ይከራከራል:: እንዴ ያመነባቸውን ነገሮች ለማሳካት ግን የሚቆጥበው ጊዜና ጉልበት የለም፤ አስከ መጨረሻው ይገፋበታል:: ያመነበትን የሚያደርግ፣ የሰበከውን ለመኖር የሚጥር ሰው ነው::

በተግባሩ ለእኔ ዓርዓያ እንደ ነበረ ሁሉ ‹ትውስታዬ› መጽሐፉን የሚያነቡ ሁሉ ከዓርዓያነቱ ብዙ እንደሚያተርፉ አገነዘባለሁ:: ትውልዱ እንዲጠቀምበት አጋብዛለሁ::

ኃይሉ ወልደ ሰማዕት

የቀድሞው የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር ዲሬክተር





ጓደኛዬ አቶ ሚሊዮን ጽፎ ስለ አስተላለፈልን ትዝታዎች አመሰግነዋለሁ። በእርሱ መሰኪያ እንደ ቁምነገር ያልቆጠራቸው፣ ያልጻፈልንም ብዙ ነገሮች እንዳሉ ይሰማኛል:: ገጣሚም ባልሆን በሚከተሉት ሁለት ስንኞች ላጠቃለው:-

«የጥንቱ የጠዋቱ፣

ይነበብ ይጠና ታሪክ ሕይወቱ»::

ከ በየነ ጭምጭይበሉ(ፒ ኤች ዲ)

ዲንና ተባባሪ ፕሮፌሰር

የድኅረ ምረቃ ት/ቤት አለማያ ዩኒቨርስቲ

ይህ የጋሽ ሚሊዮን የትውስታ መጽሐፍ ጌታ አምላካችን በግለሰቦች አልፎ ሕይወታቸውን ለውጦና ለወግ ለማዕረግ ያበቃቸው ወገኖች እነሱም በምላሹ ለአምላካቸው ክብር የሚገባወው ሁሉና አቅማቸው የፈቀደውን ሁሉ አድርገው ማለፋቸው ዛሬ ላለነው ወንጌላውያን ማሕበረሰብ ትልቅ አርዓያነት እንደ አለው ተረድቻለሁ::

በተጨማሪም:- ጌታ እግዚአብሔር በጋሽ ሚሊዮን ሕይወት ውስጥ ወንጌል ያደረገውን መልካም ነገር ለማወቅ የሚረዳ ብቻ ሳይሆን ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚገባውን ኑሮና አገልግሎት አገልግሎ ማለፍ ታላቅ ነገር እንደሆነና «በእኔና የክርስትና ሕይወት ጉዞዬ» ለአምላክ ክብር ትርጉም ያለው ሕይወትና አገልግሎት አገልግዬ የማልፈው ምን ይሆን? የሚልል ጥያቄ የሚያጭርብን ይሆናል::

ሰው ሁሉ ሊያነበው የሚገባ መጽሐፍ ነው እላለሁ::

መጋቢ. ጌታነህ አየለ

ምሥራቅ አዲስ አበባ መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን

የአቶ ሚሊዮን ትውስታዬ መጽሐፍ ተጽፎና ታትሞ ለንባብ መቅረቡ በጣም አስደስቶኛል:: ሳይጻፍም በፊት ሕይወቱንና ታሪኩን በቁም ስከታተለው ስለኖርኩ፣ እንዲጻፍም ከጎትጓቾቹ አንዱ ስለሆንኩ ተከናውኖ ማየቱ በራሱ እርካታ ሰጥቶኛል::

አቶ ሚሊዮንን መጀመሪያ ያየሁት ያኔ ከአሜሪካ ተመልሶ ከዶ/ር በየነ ጭምጭ አይበሉ ጋር ሆነው ወደ ሻሸመኔ በመጡበት አጋጣሚ ነበር:: ያኔ እኔ የ17 ዓመት ጎረምሳ ነበርኩ:: ያስተማሩንን ነገር ለመመዘን በቂ አውቀት ባይኖረኝም፣ በሁኔታቸውና በንግግራቸው መመሰጤ ትዝ ይለኛል::

እነርሱን በማየቴ «ለካንስ እንደ እነርሱ መሆን ይቻላል» ለማለት አስችሎኛል::

የጋሽ ሚሊዮን ሕይወት ከሕይወቴ ጋር በመልካም ተሳስሮ የኖረ ከመሆኑም በላይ በእየለቱ ስማርበት የኖርኩት የሆንኩት ሰው በዚህ መጽሐፍ ተጠቃሎ፣ ለቀጣዩ ትውልድ መቅረቡ አስደስቶኛል::

ለቀጣዩ ትውልድ ይህን ምስክርነት ለማቅረብ በመቻልህ ጋሽሚሊዮን እንኳን ደስ ያለህ::

ዶ/ር ተስፋጸዮን ደለለው

. . መጽሐፉ በአርትኦት አልፎ ለሕትመት ከመውጣቱ በፊት አፍታውን ቀምሼ "ለካ የአገርም ታሪክ በአንድ ሰው ታሪክ በኩል ሊነገር ይችላል" አልኩ፤ ይህንን አባባል አንባቢም እንደሚደግመው አልጠራጠርም።

ሰሎሞን ጥላሁን
(ከአሜሪካ ቨርጂኒያ)

. . . ብዙ ጊዜ፦ «ከታሪክ የማይማር፣» ወይም «ከታሪክ አለመማር» ወይም «ከታሪክ መማር» የሚሉት ሐረጎች ተደጋግመው ይነገራሉ፤ ትክክል ነው፡፡ ግለሰብ፣ ማኅበረሰብ፣ ቤተ ክርስቲያን፣ ሕዝብ ወዘተ፣ በታሪክ መስተዋት ያለፉበትን ሁሉ እያዩ ስህተትን ከመድገም ይጠበቃሉ። አልፎም ወደ ስኬት ጎዳና ወይም ወደ ድል ጎዳና ያመራሉ፤ ወደ ውጤታማነትም ያቀናሉ።

ማሞ ገብረ መስቀል
(የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የቀድሞ የቦርድ ሰብሳቢ)

. . ጋሽ ሚሊዮንን በደንብ «አውቀዋለሁ» ብዬ የማምን ሰው ነበርኩ። የሕይወት ታሪኩን «ትውስታዬ»ን ረቂቅ ካነበብኩ በኋላ ግን፤ ከዚህ በፊት ስለ እርሱ የነበረኝ ዕውቀት እጅግ በጣም አነስተኛ እንደነበረ ተገነዘብኩ። «ትውስታዬ» እርሱን የመሰለ ወንድም የሰጠንን ጌታ እጅግ በጣም እንዳመሰግነው ምክንያት ሆናኛለች።

(መለሰ ወጉ)

«ትውስታዬ» በተሰኘው መጽሐፉ ጋሼ ሚሊዮን በለጠ ከልጅነቱ እስከ ሽበት ማውጣት የተሸከመው ጌታ ያደረገለትን ዋና ዋና ጉዳዮችን እያወሳ ሊያስነብበን ቀርቧል። በጠቅላላ ልብ አንጠልጣይ ነው። ከትንሽ ጅማሬ ተነስቶ ትልልቅና አበይት የሆኑ ክንዉኖችን እንዲያደርግ የረዳውን ጌታ እጅና ምሪትን በሕይወቱ አይቼበታለሁ።

በድሩ ሁሴን

ይህ የጋሽ ሚሊዮን የትውስታ መጽሐፍ . . . ዛሬ ላለነው ወንጌላውያን ማሕበረሰብ ትልቅ አርዓያነት እንደ አለው ተረድቻለሁ፡፡

መጋቢ ጌታነህ አየለ
(ምሥራቅ አዲስ አበባ መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን)

አቶ ሚሊዮንን መጀመሪያ ያየሁት ያኔ ከአሜሪካ ተመልሶ ከዶ/ር በየነ ጭምጮ አይበሉ ጋር ሆነው ወደ ሻሸመኔ በመጡበት አጋጣሚ ነበር፡፡ ያኔ እኔ የ17 ዓመት ጎረምሳ ነበርኩ፡፡ ... እነርሱን በማየቴ «ለካንስ አንደ እነርሱ መሆን ይቻላል» ለማለት አስችሎኛል፡፡

(ዶ/ር ተስፋጽዮን ደለለው)

በአሜሪካ የሚሊዮን "ትውስታዬ" ጓደኛችን እንግዳ አስፋው (አሁን ዶር.) እንዳለው
Only one life, it will soon be past. What is done for Christ will last-
አንድ ሕይወት ብቻ አለ. እርሱም ያልፋል፤ ለክርስቶስ የተሠራ ይዘልቃል።
ትውስታዬን እንበቢት፣ ትባረካላችሁ።

ፀጋ ወልደማርያም (ኢንጅነር)

ዋጋ 100 ብር
$ 20 ዶላር